# ምዕራፍ 11

# አንድ ዓለማዊነት

«...የፈረሶቻቸውም ኮቴ እንደ ቡላድ የሰረገሎቻቸውም መንኮራኩር እንደ ዐውሎ ነፋስ ይቆጠራል:: ጩኸታቸው እንደ አንበሳ ነው፣ እንደ አንበሳ ደቦሎችም ያገሣሉ ንጥቂያውንም ይዘው ያገሣሉ፣ ይወስዱትማል፣ የሚያድንም የለም::»

(ትንቢተ ኢሳይያስ 5:28-)

ስለ አዲስ ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት፣ አዲስ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት እንዲሁም በቅርቡ ልንደርስበት እንደምንችል ስለሚነገረን አዲ የዓለም ሥርዓት በየጊዜው ይበልጥ እየሰማንና እያወቅን ያለ እንዲሁ በአጋጣሚ አይደለም:: ወደዚሁ «አዲስ ሥርዓት» የሚደረ ግስጋሴ ጥቂት ለማይባሉ ዐሥርተ-ዓመታት በጥንቃቄ የታቀደ ነ በአሁኑ ወቅት ማንኛውንም ዓለም አቀፋዊ ችግር፣ አሳሳቢ ነገ ፍላጎት የሚያስተናግዱ የተለያዩ ድርጅቶች እስኪቋቋሙ ድረስ በ ረገድ በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፣ ተቋማትም ተመሥርተዋ በተለያዩ የመጓጓዣ ዘዴዎች ምክንያት ዓለማችን አንድ መን እየሆነች ነው፤ ኢንተርኔትም በዚህ ረገድ የሚጫወተው ትልቅ ሚ አለ:: ሀገራት እርስ በርስ በሚካሄድ ንግድ ይበልጥ እየተሳ መጥተዋል፤ ጥሬ እቃ፣ ምግብና ነዳጅ ዘይት የመሰሉ የኃ ምንጮችን በመለዋወጥ እርስ በርስ እየተደጋገፉ ነው:: ሀገ በትምህርት፣ ባህልና ሳይንስ ዘርፎች መተባበራቸው ይበልጥ እ በርስ አስተሳስሯቸዋል:: ይህ ሁሉ የአንድ የሰው ዘር አባ እንደሆንን አጽንኦት የሚሰጥ ነው:: የዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖትና ባ ልዩነቶቻችን በጋራ ሥረ-መሠረት፣ አካባቢ፣ ፍላጎትና ም እየተዋጡ ነው::

ስለዚህም፣ «እጅ ለእጅ ተያይዘን ቀሪዎቹን ገደቦች አስወግ አንድ እንሁን:: ሁላችንም በአንድ ጣሪያ ሥር እንሁን:: ማንኛው ነገር የጋራችን ይሁን» የሚል ምክር በተለያየ መልኩ በመላው ዓለ ዙሪያ እየተደመጠ ነው:: በእርግጥ፣ አዲስ የዓለም ሥር

ለመመሥረት ቀሪዎቹ ዕንቅፋቶችና መሰናክሎች መወገድ አለባቸው:: ይህ እውን እንደሆነ ደግሞ ሁላችንም «የምድሪቷን ፍሬ» መካፈል የምንችልበት አዲስ የዓለም መንግሥት ሊኖረን ይገባል::

ነገርየው በዚህ መልኩ ሲቀርብ ማራኪ ይመስላል:: «ኃይል 13 የሚጫተው ሚናስ?» ብለን ብንጠይቅ ደግሞ የምናገኘው ምላሽ፣ «አጉል እምነት ነው:: በሰይጣን የሚያምን ማን አለ? የወደፊት ሕይወታችንን ልንገነባበት ወይም ልናበላሽበት የምንችለው ዐቅም በእጃችን ውስጥ ነው» የሚል ነው::

ሥልጣንን እጁ ውስጥ ያደረገው ሰው በዚህ አባባል እምነት ሊያድርበትና ይህንኑ ሊያሰራጭ ይችላል:: ይሁንና፣ ተራው ሕዝብ በዚህ ረገድ እርግጠኛ አይደለም:: ስለዚህም፣ ሌሎች ያሉትን ወይም ያቀረቡለትን ይከተላል:: መንገዱን የሚመራው ካገኘ ትክክል ነው ብሎ በማሰብ በዚህ ጉዳና ይጓዛል:: በቀን ሦስት ጊዜ ከተመገበና ጥቂት መገልገያና መጫወቻ እቃዎችን ካገኘ፣ በአንድ ዓለም ባቡር ላይ በነጻ ተሳፍሮ ቢጓዝ ግድ የለውም::

በአሁኑ ዘመን በአዲስ ዓለም ፈጣን ባቡሩ ላይ በርካታ ታዋቂና ጉዞው አስደስቷቸው ብቻ የተሳፈሩ ተራ ሰዎች አሉበት:: በጣም ረዥም ባይሆንም፣ ጉዞው አስደሳች ነው ብለን ማሰብ የለብንም:: በ1776 ዓ.ም. ጉዞውን የጀመረው ባቡር አሁንም ድረስ ተሳፋሪዎችን እያሳፈረ ነው:: ይህንንም ማመን ይኖርብናል:: ምሥጢር መሆኑ ቀርቶ በግልጽ የሚታይ ሴራ እየሆነ ነው:: ምሁሯና ደራሲዋ ሜሪ ፈርጉሰን ዘ አኳሪየን ኮንስፒረሲ መጽሐፏ ላይ ሁኔታውን «ቀስ በቀስ የሰው ልጅን የሚሸረሽር ሴራ» ብለዋለች::

## የጎርባቼቭ ራእይ

ሚኻኢል ጎርባቼቭ በታኅሣሥ 1988 ዓ.ም. በተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ላይ ለመገኘት ወደ ኒው ዮርክ ተጉዘው ነበር:: ታይም መጽሔት ይህን ተከትሎ ባወጣው ዘገባ፣ «ሚኻኤል ጎርባቼቭ ለ21ኛው ምዕተ-ዓመት 'አዲስ የዓለም ሥርዓት' ራእይ ይዘው ብቅ ብለዋል:: ባለፈው ሳምንት ለተባበሩት መንግሥታት ባደረጉት ድንቅ ንግግር፣ የሶቪዬቱ ፕሬዚዳንት የወታደራዊ ኃይል ስጋት የውጭ



Scanned with CamScanner

ግንኙነት ፖሊሲ መሣሪያነቱ እንደሚያበቃና ርዕዮተ-ዓለም በሀገራት መካከል በሚኖረው ግንኙነት የሚጫወተው ሚና እጅጉን እንደሚቀንስ በመግለጽ የወደፊቷ ዓለም ምን እንደምትመስል የራሳቸውን ሥዕል ሥለውልናል:: ይህ ጠንካራና ድፍረትን የተላበሰ ራእያቸው በጦር መሣሪያ ላይ ከተመሠረተ ኢኮኖሚ የጦር መሣሪያ ቅነሳን ዋና ትኩረቱ ወደ አደረገ ኢኮኖሚ የሚደረግን ሽግግር ጠቋሚ ነው» ብሏል::

እንግዲህ የጎርባቼቭ ራእይ የጦር መሣሪያዎች ዓቢይ ሚና የማይጫወቱበት አዲስ የዓለም ሥርዓት ነው:: የመጨረሻው እቅድም የጦር መሣሪያዎችን በሙሉ በማወድም ሀገራት በአዲስ ዓለም ድርጅት በኩል የዓለምን ችግር ለመፍታት በጋራ እንዲሠሩ ነው::

## የዴንግ ራእይ

የወቅቱ የሕንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ራጂቭ ጋንዲ በታኅሣሥ 1988 ዓ.ም. ከሊቀመንበር ዴንግ ዚአኦፒንግ ጋር ተገናኝተው የተነጋገሩበትን ቻይና ጐብኝተዋል:: ራጂቭ ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ ጋዜጠኞች፣ «ቻይና ውስጥ ይበልጥ ስሜትዎን የነካው ነገር ምንድን ነው?» የሚል ጥያቄ አቅርበውላቸው ነበር:: ራጂቭ ለጥያቄው የሰጡት ምላሽ፣ «ቻይና ውስጥ ስሜቴን ይበልጥ የነካው የዴንግ ዚአኦፒንግ የአዲስ ዓለም ሥርዓት ራእይ ነው» የሚል ነበር::

## የቡሽ ራእይ

የቀድሞው የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፕሬዚዳንት ጆርጅ ቡሽ «አዲስ ዓለም ሥርዓት» የሚለውን ሐረግ በተደጋጋሚ በመጥቀስ በሕዝብ ዘንድ እንዲታወቅ አድርገዋል:: ፕሬዚዳንቱ ለዕረፍት በሜይን ግዛት ውስጥ በተገኙበት ወቅት በፋርስ ባሕረ-ሰላጤ ከተፈጠረው ውጥረት ይልቅ ሌላ ነገር በአእምሯቸው እያሰላሰሉ ነበር:: ቡሽ ዓሣ እያጠመዱና ጎልፍ እየተጫወቱ ስለ ድኅረ-ቀዝቃዛው ጦርነት በሚያሰላስሉበት ሜይን ስለ አዲስ የዓለም ሥርዓት ያውጠነጥኑ ነበር::

አንድ አማካሪያቸው፣ «የፕሬዚዳንቱ ራእይ ጆን ፎስተር ዱለስን በተቀመጠበት በድንጋጤ የሚያደነዝዝ ዓይነት ነው:: ራእያቸውም ዩ.ኤስ. አሜሪካና ሶቪዬት ኅብረት በመላው ዓለም ዙሪያ ያሉትን ችግሮች ለመቆጣጠር የሚተባበሩበት ነው» ሲል ተናግሯል::



Scanned with CamScanner

ፕሬዚዳንቱ ለኮንግሬስ ባቀረቡት ንግግር ራእያቸውን ለአሜሪካ ሕዝብ ይፋ አድርገዋል፡፡ «ሁላችሁም እንደምታውቁት፣ በጣም ውጤታማ የሆነ ስብሰባ ከሶቪዬቱ ፕሬዚዳንት ጎርባቼቭ ጋር አድርጌ ተመልሻለሁ፡፡ አዲስ ግንኙነት ለመገንባት በጋራ እየሠራን በመሆናችን ደስተኛ ነኝ... አዲስ የሀገራት ሽርክና ተጀምሯል፡፡ በፋርስ ባሕረ-ሰላጤ የተፈጠረው ቀውስ እጅግ አሳሳቢ ቢሆንም፣ ታሪካዊ ወደሆነ የትብብር ወቅት እንድንሸጋገር እምብዛም የማይገኝ ዕድል ፈጥሮልናል፡፡

«ከዚህ ቀውጢ ወቅት አምስተኛው ዓላማችን፣ ማለትም አዲስ የዓለም ሥርዓት፣ ብቅ ሊል ይችላል፡፡ ይህም ዘመን ከሽብር ስጋት ነጻ የሆነ፣ ፍትሕ ለማስፈን የበለጠ ጥንካሬ የሚገኝበትና ሰላምን በሚመለከት ይበልጥ አስተማማኝ የሆነበት ነው፡፡ በምሥራቅና ምዕራብ፣ በሰሜንና ደቡብ የሚገኙ ሀገራት የሚበለጽጉበትና በስምምነት የሚኖሩበት ዘመን ነው፡፡

«በመቶዎች የሚቆጠሩ ትውልዶች ይህን የማይጨበጥ የሰላም መንገድ ሲፈልጉ አልፈዋል፡፡ በሺህ የሚቆጠሩ ጦርነቶችም ለሰው ልጅ እድገት ዕንቅፋት ሆነዋል፡፡ ዛሬ ደግሞ አዲስ ዓለም ሊወለድ እያማጠ ነው፡፡

«ይህም ዓለም እኛ ከምናውቀው ጋር ሲነጻጸር ፍጹም ነው፡፡ የጫካ ሕግ በሕግ የበላይነት የሚተካበት፣ ሀገራት ነጻነትንና ፍትሕን በሚመለከት የጋራ ኃላፊነት የሚቀበሉበት ዓለም ይሆናል፡፡

«ጠንካሮች የደካሞችን መብት የሚያከብሩበት ዓለም ይሆናል፡፡ ሄልሲንኪ ቆይታዬ ከፕሬዚዳንት ጎርባቼቭ ጋር የተጋራሁት ይህን ራእይ ነው፡፡ ጎርባቼቭ፣ እንዲሁም የአውሮጳ፣ የባሕር ሰላጤው ሀገራትና በመላው ዓለም ዙሪያ በሚገኙ ሀገራት ያሉ ሌሎች መሪዎች አሁኑ ወቅት ያጋጠመንን ችግር የምንቆጣጠርበት መንገድ መጪዎቹን ትውልዶች መጻኢ ዕድል ቅርጽ እንደሚያስይዝ ተረድተዋል፡፡»

ይህ አዲስ የዓለም ሥርዓታቸው ምን ዓይነት ቅርጽ ይኖረዋል? የቡሽ አስተዳደር አዲስ የዓለም ሥርዓት የመገንባት እቅድ ተባበሩት መንግሥታትን የማእዘን ድንጋይ ማድረግ ይፈልጋል፡፡»



Scanned with CamScanner

ፕሬዚዳንት ቡሽ የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት እንደተጀመረ ለዓለም ሕዝብ ባደረጉት ንግግር፣ «ይህ ውጊያ ለረዥም ጊዜ እንደማይቀጥል ጉዳት የሚደርስባቸው ሰዎች ቁጥር ዝቅተኛ እንደሚሆን ተስፋ አለኝ። በአንድ ታሪካዊ ወቅት ላይ እንገኛለን:: ባለፈው ዓመት ረዥም የግጭትና የቀዝቃዛ ጦርነት ወቅት በመቋጨት ትልቅ እድገት አስመዝግበናል:: ለራሳችንና ለመጪዎቹ ትውልዶች የጫካ ሕግ ሳይሆን የሕግ የበላይነት የሀገራትን እንቅስቃሴ የሚመራበት አዲ የዓለም ሥርዓት ለመመሥረት ዕድሉን አግኝተናል:: በዚህ ረገ ስኬታማ ከሆንን፣ እንሆናለንም፣ እምነት የሚጣልበት የተባበሩት መንግሥታት ሰላም የማስከበር ሚናውን የድርጅቱ መሥራቾች የገቡትን ቃል ለማሟላት የሚጠቀምበት አዲስ የዓለም ሥርዓ ለመመሥረት እውነተኛ ዕድሉ አለን::»

## የአውስትራሊያ ሚና

የቀድሞው የአውስትራሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦብ ሆውክ የጆርጅ ቡሽን አስተያየት እንዲህ ሲሉ አስተጋብተዋል:: «ከውሳኔያችን (ኢራቅን የመውጋት) በስተጀርባ ሰፊ ዓላማ አለን:: ዓላማው ከነሐሴ ቀን ጀምሮ የተባበሩት መንግሥታት ባደረገው ነገር ሁ የተንጸባረቀ ነው:: ይህም ዓላማ በዩ.ኤስ. አሜሪካና ሶቪዬት ኅብረ መካከል የነበረው ፍጥጫ እንዳበቃ ከዚህ ብቅ ያሉትን ሰላ ደኅንነትና ነጻነት፣ ተስፋና ዕድል እውን የሚያደርግ አዲስ የዓለ ሥርዓት ምሥረታን ማፋጠን ነው::»

የተለያዩ ሀገራት መሪዎች የተወሰነ ዓይነት አዲስ የዓለም ሥርዓ ምሥረታን በመደገፍ ድምፃቸውን እያሰሙ ነው:: በእርግ ጎርባቼቭ፣ ዴንግ፣ ቡሽ፣ ሆውክና መሰሎቻቸው በዓይነ-ኅሊናቸ ያሰቡት አዲስ የዓለም ሥርዓት ዌይስሆፕት፣ ኃይል 13 እና ው ዐወቆቹ ካዘጋጁት እቅድ ጋር ፍጹም አይገናኝም የሚሉ ወገኖች አሉ

## ምን ዓይነት አዲስ የዓለም ሥርዓት?

አዲስ የዓለም ሥርዓት እንደሚያስፈልገን የታወቀ ነው:: ይሁ መጠበቅ ያለብን ምን ዓይነት ሥርዓት ነው? የሰላም ልዑል የሆ ክርስቶስ ተቀባይነትን ሳያገኝ ከሰብአዊ ኃይልና ከጦር መሣሪያ

የተገነባ ሌላ ዓለም እንዴት ልንጠብቅ እንችላለን? ንግድን የሚመለከቱ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ መርሖዎች እየተረገጡ ትክክለኛ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት እንዴት ልንጠብቅ እንችላለን? መለኮታዊ፣ የግብረ-ገባዊና ማኅበራዊ መመሪያዎች እየተጣሱ ከዚህ ምን ይገኛል ብለን እንጠብቃለን?

የሰው ልጅ የሚስፈልገው እውነተኛ ሰላም፣ ፍትሕ፣ እውነትና ቅዱስነት የሰፈነበት የዓለም ሥርዓት ነው። አዲሱ የዓለም ሥርዓት የታማኝነት፣ መከባበር፣ ልግስና፣ ፍቅርና ጽድቅ መንፈሳዊ ሥርዓቶችን በየጊዜው የምንማርበትና ተግባራዊ የምናደርግበት መሆን አለበት።

የጆርጅ ቡሽን አዲስ የዓለም ሥርዓት ከተቃወሙት መካከል አንዱ ኪሲንጀር ናቸው። ምሥረታውን እውን ማድረግ የማይቻል ነው የሚሉት ኪሲንጀር፣ «አዲሱ የዓለም ሥርዓት ፕሬዚዳንቱ የገለጿቸውን ሐሳቦች ማሟላት አይችልም። የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፖሊሲ አውጪዎች አዲሱ የዓለም ሥርዓት አሜሪካ ባስቀመጠቻቸው መመዘኛዎች መገንባት እንደማይችል ሊገነዘቡት ይገባል። አሜሪካ ምንም ዓይነት መሠረት በሌለበት ዓለም ውስጥ በዓለም አቀፍ ደረጃ የማኅበረሰባዊነትን ስሜት በግድ መፍጠር አትችልም። «የጋራ ኃይልን» በሚመለከት ተስፋ ያደረጉ ወገኖች በመንግሥታቱ ማኅበርና በተባበሩት መንግሥታት ቅር ተሰኝተዋል» በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በእርግጥ፣ ኪሲንጀር ትክክል ናቸው። አዲሱ የዓለም ሥርዓት በምኞት ደረጃ የምናስባቸውን ነገሮች የሚያሟላ አይደለም። ይሁን እንጂ፣ ሰይጣናዊ ፍላጎትንና ምኞትን የሚሟላት ጥሩ ዕድል አለው። በሌላ በኩል፣ የክርስቶስ ተቃዋሚ ግዛት ማእከል አውሮጳ እንጂ አሜሪካ አይደለችም። ስለዚህም፣ በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 13 ላይ የተተነበየውን ዓለም አቀፍ አምባገነናዊ ሥርዓት እውን በማድረጉ በኩል የሚሳካለት አውሬው ለማቋቋም የረዳው አዲስ የዓለም ሥርዓት ብቻ ነው።

ለሰው ልጅ የሚበጀውና የሚጠቅመው አዲስ የዓለም ሥርዓት መመራት ያለበት በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ ተሰቅሎ የሞተው



Scanned with CamScanner

የመላውን የሰው ልጅ ኃጢአት ለማንጻት ነው። «ክርስቶስንም ከሙታን ሲያስነሣው እግዚአብሔር ለአለቅነትና ከሥልጣንም ከኃይልም ከጌትነትም ሁሉ በላይ በሰማያዊ ስፍራ በቀኙ ሲያስቀምጠው በክርስቶስ ባደረገው ሥራ የብርታቱ ጉልበት ይታያል፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ በላይ ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው።» (ወደ ኤፌሶን ሰዎች 1:20-22)

Scanned with CamScanner

## ምዕራፍ 12

# ምሥጢራዊ ዘዴዎች

«እንደ ስሕተት ሽንገላ ባለ ተንኰሉ በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያ ወዲህም እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደፊት አይገባንም።፡»

(ወደ ኤፌሶን ሰዎች 4:14)

ቅንጣት ታክል እውነት ወስደን አጋንነንና አጉልተን ብናቀርበው ውሸት ብቻ ሳይሆን ሰው ሠራሽ ችግርም እንፈጥራለን:: ሴረኞች ከጥንት ጀምሮ እየተጠቀሙበት ያለና በአሁኑ ዘመን አስገራሚ ውጤት እያስገኘ ያለ ቀላሉ ቀመር ይኸው ነው::

አንድ ነጋዴ በሚሊዮን የሚቆጠር ሳሙና አከማችቶ ሲያበቃ በሚፈጠረው የሸቀጡ እጥረት ሕዝቡ እጥፍ ዋጋ ለመክፈል መገደዱ በራሱ መጥፎ አካሄድ ነው:: ይሁንና፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰው ሠራሽ ችግር ሲፈጠር መጠነ-ሰፊ ሽብርን፣ እንዲሁም ሰዎችና ሀገራት መሠረታዊ ፍላጎታቸውን ለውጭ ቁጥጥር አሳልፈው መስጠት ይከተላል::

ሰይጣን በዚህ ዓይነቱ አሠራር ቀንደኛ ነበር፣ አሁንም ነው:: በአንድ ግለሰብ ሕይወት ውስጥ የተፈጠረውን ችግር ነጥሎ በማውጣት «መፍትሔ» ያለውን ሐሳብ አእምሮው ውስጥ ያሳድርበታል:: መፍትሔው ግን ግለሰቡን ይበልጥ በሰይጣን መዳፍ ሥር የሚከትተው ነው::

ለምሳሌ፣ ነጭናጫ ሚስት ያለው አንድ ሰው አለ እንበል:: ሰይጣን ለችግሩ እንደ መፍትሔ የሚያቀርብለት «ጭንቀቱን የሚያስረሳለትን» አልኮል መጠጥ ይሆናል:: ይሁንና፣ ግለሰቡ ከመፍትሔው የሚያተርፈው ነገር ቢኖር ሱሰኝነትን፣ የገንዘብ ኪሳራን፣ ድካምን፣ ተጨማሪ ንጭንጭን፣ የጤና መታወክንና ውድቀትን ነው::

የብቸኝነት ችግር ያለባት አንዲት ሴት አለች እንበል:: ሰይጣንም «ራስሽን አስደስቺ» በማለት ሴሰኝነትን እንደ መፍትሔ

ያቀርብላታል:: ልጅቷ ችግሯን ከማቃለል ይልቅ የጥፋተኛ ስሜት፣ ፍርሃት፣ ተስፋ መቁረጥና በሽታ ለመሰሉ ተጨማሪ ችግሮች ትጋለጣለች::

የገንዘብ እጥረት ያለበት አንድ ሰው አለ እንበል:: ሰይጣንም፣ «በሌሎች ሀብት ተጠቀም» ሲል ይመክረዋል:: ግለሰቡ ማጭበርበር፣ ስርቆት፣ ዘረፋ ወደመሰሉ ወንጀሎች በማምራት ለእስራት ይዳረጋል:: ይህን ጊዜ በሚፈጠሩት የመንፈስ መረበሽና ሽንፈት ሰይጣን ይረካል::

ዝና ቢኖራትም፣ በተደጋጋሚ የመሠረተቻቸው ትዳሮች በፍቺ ሲጠናቀቁ ባደረባት የጥፋተኝነት ስሜት፣ ብቸኝነትና ቀቢጸ-ተስፋነት በከባድ የመደበት ስሜት የምትሠቃይ የፊልም ተዋናይት አለች እንበል:: ሰይጣን፣ «የሽጉጡን ቃታ ስበሽ ራስሽን ካጠፋሽ ዓለም ሁሉ ያለቅስልሻል፣ አንቺም ከችግርሽ ትላቀቂያለሽ» በማለት መፍትሔ ይጠቁማታል:: ይሁንና፣ ከድርጊቷ የምታገኘው ውጤት ሞት፣ ጸጸት፣ ገሃነም፣ ዘለዓለማዊ የሰይጣን ቁጣ፣ እንዲሁም የዘመድ ወዳጆቿን ለቅሶ፣ ዋይታና ጥርስ ማፋጨት ነው:: ሰይጣን ግን ሐሳቡን አሳክቷል::

ሰይጣን የግለሰቦችን ችግር ለዓላማው ማስፈጸሚያነት እንደሚጠቀምበት ሁሉ የዓለምንም ፍላጎት ወደ ቀውስ በመለወጥ ሀገራትን ያንበረክክበታል:: ዓለም አቀፍ ባንከኞች ደግሞ የገንዘብ እንቅስቃሴን በማሳደግ ወይም በመቀነስ የዋጋ ግሸበት ወይም ንረት በመፍጠሩ ረገድ የተካኑ ናቸው:: ከዚህ በተጨማሪም፣ መንግሥታትን በመገልበጥና የጦርነት ወጪዎችን በመሸፈን ፖለቲካውን እንዳሻቸው ያሽከረክሩታል:: በአሁኑ ዘመን ደግሞ ከውስጠ-ዐወቆቹ ጋር በመተባበር ሀገራት ተስፋቸው የዓለም መንግሥት ነው ከሚል ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ሰው ሠራሽ ችግር እየፈጠሩ የዓለማችንን ሁኔታ ለራሳቸው ዓላማ ማስፈጸሚያነት ይጠቀሙበታል::

የምንኖርባት ዓለም ችግሮች እንዳሉባት የሚካድ አይደለም:: ከብዙ በጥቂቱ የኑክሊየር ጦር መሣሪያዎች ግንባታ፣ የሕዝብ ብዛት፣ ረሃብ፣ ብክለት፣ የኃይል እጥረት፣ ወንጀል፣ አደንዛዥ ዕፅና ተጠቃሾች ናቸው:: እነኝህን ችግሮች ለመቅረፍ ዓለም አቀፋዊ ትብብር እንደሚያስፈልግ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው:: ፈንጣጣ

ለመቆጣጠር የተቻለው የዓለም ጤና ድርጅትን የመሰሉ በርካታ ድርጅቶች ያለጥርጥር ጥሩ ሥራ ስላከናወኑ ነው:: በርካታ ምናልባትም አብዛኞቹ የዓለም አቀፋዊነት መርሕ አራማጆችም ድብቅ ዓላማ ሳይኖራቸው ለሰው ልጅ እድገት እየሠሩ ነው:: ዓለምን መግዛት ከሚፈልጉት ድርጅቶች በስተጀርባ ያሉት የሴራው ውስጠ-ዐወቆች ናቸው:: ከነሱም በስተጀርባ ኃይል 13 አለ::

ሰይጣን «ጥሩ ፍጡር» ቢሆን ኖሮ፣ ምንም የሚያስጨንቀንና የሚያሳስበን ነገር ባልኖረ ነበር:: ዳሩ ግን፣ ያለምክንያት የ«13» ቁጥር ማኅተም አላረፈበትም:: ተነግሮ የማያልቅ መከራና ሥቃይ ባስከተለባቸው ያለፉት 6000 ዓመታት የፈጸመው ድርጊት በሚገባ ተመዝግቧል:: ሥራውን ከመጨረሱም በፊት የሚችለውን ያህል ጥፋት ማስከተሉ አይቀርም:: ለዚህ ዓላማው ማስፈጸሚያነት ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎቹ መካከል የጦር መሣሪያ ግንባታ አንዱ ነው::

## የጦር መሣሪያ ግንባታ

ዓለማችን በየደቂቃው $2 ሚሊዮን ለጦር መሣሪያ ግንባታ ታወጣለች፤ ይህም የገንዘብ መጠን በየጊዜው እንደጨመረ ነው:: ከሔይን ከተባለው አደንዛዥ ዕፅ ንግድ ቀጥሎ ጦር መሣሪያ የዓለማችን ትልቁ የንግድ ዘርፍ ነው:: ጦር መሣሪያ ማከማቸት፣ በተለይም ዓለማችንን በተደጋጋሚ ብዙ ጊዜ ማጥፋት የሚችሉ በቂ ጅምላ ጨራሽ መሣሪያዎች መኖራቸው፣ ችግር እንደሚፈጥር መካድ አይቻልም::

የጦር መሣሪያ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ወጪን ማን እንደሚሸፍነው ግልጽ ነው:: የዓለም ሀገራት እነኝህን የጥፋት መሣሪያዎች ለመገንባት ወይም ለመግዛት የሚያስፈልጋቸውን ብድር ሚሰጧቸው ዓለም አቀፍ ባንኮች ናቸው:: የጦር መሣሪያ ግንባታም ን ግዝ ለዓለማችን ሕዝብ አስፈሪ ችግር መፍጠሩ የማይታበል ሐቅ ው::

ለችግሩ መፍትሔ ስላለው ግን ልንጨነቅ አይገባም:: ካስፈለገን፣ ፍትሔ 13 ብለን ልንጠራው እንችላለን:: መፍትሔውም የጦር ሣሪያ ቅነሳ ነው:: የዓለማችን ሕዝብ ትጥቁን ከፈታ፣ ማንም ሰው



Scanned with CamScanner

ጦርነት መፍጠር አይችልም! ዩ.ኤስ. አሜሪካና ሩሲያ የሚደራደሩበት የእስትራቴጂክ ጦር መሣሪያዎች ቅነሳ ድርድር ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት እንደሆነ ይነግሩናል፡፡

የዓለማችን የጦር መሣሪያዎች በሙሉ ቢጠፉ፣ «ሃሌሉያ!» ብለን በደስታ በጮኽን ነበር፡፡ ዳሩ ግን፣ የዛሬ ዘመን «የጦር መሣሪያ ቅነሳ» የጦር መሣሪያ የሌለበት ዓለም ማለት አይደለም፡፡

ሶቪዬት ኅብረት በመስከረም 1960 ዓ.ም. «የተሟላና አጠቃላይ የጦር መሣሪያ ቅነሳን» በሚመለከት ለተባበሩት መንግሥታት አንድ እቅድ ታቀርባለች፣ እቅዱ ሥርዓትን የተከተለ የጦር መሣሪያ ቅነሳን የሚጠይቅ ነበር፡፡ ከጥቂት ወራት በኋላ የውጭ ግንኙነት ካውንስል ዩ.ኤስ. አሜሪካ «ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት መፈለግ... የተባበሩት መንግሥታትን ሥልጣን መያዝና ይህንኑ ቀስ በቀስ ማሳደግ... በጦር መሣሪያ ገደብ፣ ቅነሳና ቁጥጥር ዙሪያ ዓለም አቀፋዊ ስምምነት ለማግኘት ጠንከር ያሉ ድርድሮችን መምራት» እንዳለባት የሚያትተውን «ጥናት ቁጥር 7» አውጥቷል፡፡

በቀጣይነትም የዩ.ኤስ. አሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በመስከረም 1961 ዓ.ም. «ከጦርነት ነጻ መሆን – በሰላማዊ ዓለም አጠቃላይና የተሟላ የጦር መሣሪያ ቅነሳ የዩ.ኤስ አሜሪካ መርሐ ግብር» በሚል ርእስ ቁጥር 7277 ኅትመትን አውጥቷል፡፡ በዚህ እቅድ መሠረት፣ «በደረጃ 3 በየጊዜው ቁጥጥሩ ጠበቅ የሚል የጦር መሣሪያ ቅነሳና ያለማቋረጥ የሚዳብሩ የዓለም አቀፍ ሕግ መርሖዎችና ሥርዓቶች አንድም ሀገር በየጊዜው እየተጠናከረ የሚሄደውን የተባበሩት መንግሥታት ሰላም አስከባሪ ኃይል የሚቀናቀኑበት ወታደራዊ ኃይል እስከማይኖረውና ዓለም አቀፋዊ ግጭቶች ስምምነት ላይ በተደረሰባቸው ዓለም አቀፋዊ አሠራሮች መፈታት እስከሚችሉበት ጊዜ ድረስ ይቀጥላል... የተባበሩት መንግሥታት ሰላም የማስከበር ዐቅም የሚፈለገውን ጥንካሬ ሲያገኝና የስምምነቶቹ ተገዢ የሆኑ ሀገራት በሙሉ ግዴታቸውን ሲወጡ ሰላም የማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን የጦር መሣሪያ በሌለበት ዓለም ውስጥ የሚፈጠሩ ልዩነቶች ፍትሐዊ በሆነ መልኩ ይፈታሉ፡፡»



Scanned with CamScanner

የዩ.ኤስ. አሜሪካ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ኤጀንሲ በጥቅምት 1968 ም. «የጦር መሣሪያ ቁጥጥርና ብሔራዊ ደኅንነት» በሚል ርእስ ጣው መግለጫ የተባበሩት መንግሥታት ብቻ የጦር መሣሪያ ደሚታጠቅ በግልጽ አስቀምጧል:: መግለጫው እንደሚለው፡ 1959 ዓ.ም. ወዲህ የድርጅቶቹ የመጨረሻው ግብ አጠቃላይና ሟላ የጦር መሣሪያ ቅነሳ ነው:: በዚህም ሀገራት የውስጥ ማቸውን ለማስከበርና ለተባበሩት መንግሥታት የሰላም አስከባሪ ይል ለማቅረብ ከሚያስፈልጋቸው ውጭ ያለው የጦር መሣሪያና ር ኃይል ሙሉ በሙሉ ይወገዳል... የጦር መሣሪያ ቅነሳው ተካሄደ እያለ የተባበሩት መንግሥታት ሰላም አስከባሪ ኃይል ቋቋም ይጠናከራል:: እቅዱ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ሲሆን ደግሞ ንድም ሀገር ይህን የሰላም አስከባሪ ኃይል ከማይቀናቀንበት የጥንካሬ ረጃ ላይ ይደርሳል::»

ዩ.ኤስ. አሜሪካን በሚመለከት በውጭ ግንኙነት ካውንስል ተነደፈውን የአሜሪካ የጦር መሣሪያ ቅነሳ መርሐ-ግብር እንዲጀመር ደረገው የካውንስሉ አባል ሮበርት ማክናማራ ነው:: ማክናማራ 1961 ዓ.ም. እስከ 1968 ዓ.ም. ድረስ ባሉት ዓመታት አንድ ኑክሊየር ጥቃት ማውደም ከሚችለው የበለጠ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ስትራቴጂካዊ ጦር መሣሪያዎችን አውድሟል:: በዚህ መኻል፣ ቪዬት ኅብረት በወታደራዊ ኃይል ከዩ.ኤስ አሜሪካ እስክትበልጥ ረስ በጦር መሣሪያ ግንባታዋ ገፍታበታለች::

ከዚህ በጥንቃቄ የተዘጋጀ ያልተመጣጠነ አካሄድ በስተጀርባ ያለው ካንያት ምንድን ነው? ሉዓላዊነቱን ለአንድ ዓለም መንግሥት ሳልፎ ለመስጠት ፈቃደኛ ሳይሆን ሲቀር በሩሲያ የሚገኙት ውስጠ-ወቆች የኑክሊየር ጥቃት እንደሚሰነዝሩ ለመዛት ዕድሉን ፈጥርላቸዋል:: ከእንዲህ ዓይነቱ አደገኛ ሁኔታ ጋር የተፋጠጠው ውጭ ግንኙነት ካውንስል አባል የሆነው የዩ.ኤስ. አሜሪካ ፕሬዚዳንትም ያለምንም ጥርጥር ለዓለም መንግሥት ይንበረከካል:: ይሁንና፣ የአሜሪካን ትጥቅ እያስፈቱ ያሉት ወገኖች ሶቪዬቶች ድንገተኛ ጥቃት በመሰንዘር ዩ.ኤስ. አሜሪካን ከምድረ-ገጽ እንደማያጠፏት ምን መተማመኛ ነበራቸው? መጀመሪያ ነገር፣



Scanned with CamScanner

ሶቪዬት ኅብረት የአሜሪካ ብቻ ሳይሆን የአውሮጳ ዓለም አቀፍ ባንኮች ገንዘብ ያስፈልጋት ነበር:: ሁለተኛ ነገር፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ቀደም ሲል የሰጠቻት የቴክኖሎጂ ድጋፍና ዕውቀት ያስፈልጋት ነበር:: ሦስተኛ ነገር፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ የመሰለ ሰፊ መሬት ያላትን ሀገር ማውደሙ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል:: አራተኛ ነገር፣ ውስጠ-ዐዋቂዎቹ ያሉት በሁሉም ወገን ዘንድ በመሆኑ፣ ተግባራዊ የሚሆነው የነሱ ፍላጎት ብቻ ነው::

ዳሩ ግን፣ ውስጠ-ዐወቆቹ ጦርነት እንዳይቀሰቀስ ይከለከላሉ ማለት አይደለም:: እንዲያውም፣ ጦርነቱን የሚመለከቱት እንደ አንድ አማራጭ ነው:: ዓለም አቀፍ ባንከኞች ከዚህ ቀደም በርካታ ጦርነቶች እንዲፈጠሩ እንዳደረጉ ሁሉ፣ አሁንም አስፈላጊ ሆኖ ካገኙት ይህንኑ ከመፈጸም የሚያግዳቸው ነገር የለም:: መጽሐፍ ቅዱስ በመከራና በሥቃይ ጊዜ አንድ ትልቅ ጦርነት እንደሚቀሰቅስ ተንብይዋል:: ይህም ጦርነት ሦስተኛው የዓለም ጦርነት እንደሚሆን አምነን መቀበል አለብን:: የባሕረ-ሰላጤው ጦርነት የዚሁ ጦርነት የመጀመሪያው ምዕራፍ ነው::

በአንደኛው የዓለም ጦርነት ማግሥት የመንግሥታቱ ማኅበር ተመሥርቷል:: ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃም የተባበሩት መንግሥታት ተቋቁሟል:: ስለዚህም፣ ሦስተኛው የዓለም ጦርነት ውጤቱ በሰው 666 ፍጹማዊ አገዛዝ ሥር የሚሆን የዓለም መንግሥት ምሥረታ ነው::

በዚህ ሁሉ ሂደት የሰይጣን ዓላማ ይሳካል:: ስፍር ቁጥር የሌለው ሕዝብ ይጠፋል:: ከዚህ የከፋው ደግሞ ለረዥም ጊዜ ላቀደው ዓለም አቀፋዊ ኃኔናዊ ሥርዓት መንገዱ ይጠረግለታል::

## ምግብ፣ የሕዝብ ብዛት፣ የኃይል እጥረትና ሌሎች ችግሮች

ከኃይል 13 አማራጮች መካከል አንዱ «ከዐቅም በላይ የሆኑ ችግሮችን» በመፍጠር የዓለም መንግሥት ምሥረታን እንደ መፍትሔ ማቅረብ ነው:: ይህን አካሄድ «ወደ አዲስ ዓለም ሥርዓት የሚወስድ የችግር መንገድ» ብለን ልንጠራው እንችላለን:: እስትራቴጂው በእያንዳንዱ ሀገር ያሉትን ችግሮች ነጥሎ ማውጣትንና በዓለም አቀፋዊ ድርጅት ወይም ስምምነት መልኩ ለእያንዳንዱ ችግር «መፍትሔ» ማቅረብን የሚጠይቅ ነው::

በዚህም መሠረት፣ አብዛኞቹ በተባበሩት መንግሥታት መዋቅር ሥር የሚገኙ በርካታ ድርጅቶች ተቋቁመዋል:: አንዲት ሀገር በእነኝህ ድርጅቶች ውስጥ ይበልጥ በተሳተፈች ቁጥር ይበልጥ «ዓለም አቀፋነትን» በመላበስ የዓለማችን ሀገራት አንደኛው በሌላኛው ላይ ጥገኛ ይሆናሉ::

ከችግሮቹ መካከል አንዱ የምግብ እጥረት ነው:: የዓለም ባንክ እንዲቋቋም ጥሪውን ያስተላለፈው ሮበርት ማክናማራ በናይሮቢ በተካሄደው የዓለም ገንዘብ ድርጅት (አይ.ኤም.ኤፍ.) ስብሰባ ላይ ነው:: በኅዳር 1974 ዓ.ም. ሮም በተደረገው የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ምግብ ጉባኤ ላይ ሄንሪ ኪሲንጀር፣ «የተፋጠጠን የምግብ እጥረት ችግር ብቻ ሳይሆን አንዳችን በሌላኛችን ላይ ያለን ጥገኝነት በሚገርም ፍጥነት እየተጠናከረ መሄዱ ጭምር ነው» ሲሉ ተናግረዋል::

ዶክተር ኪሲንጀር በንግግሩ አንድ ሀገር በሌላኛው ላይ ይበልጥ ጥገኛ ነው ማለቱ ነው:: እውነታው ውስጠ-ዐወቆቹ ሀገራት በተለይ ምግብንና ኃይልን በሚመለከት አንደኛው በሌላኛው ላይ ጥገኛ እንዲሆን የሚፈልጉ መሆናቸው ነው:: ሀገራት ራሳቸውን የሚችሉ ከሆነ፣ የዓለም መንግሥት ምሥረታ ሐሳብ እንደ ነፋስ በንኖ ሊጠፋ ይችላል::

ሌላኛው ችግር የሕዝብ ብዛት ነው:: የሕዝብ ብዛት ብዙዎቻችንን የሚያሳስበን ችግር ቢሆንም፣ የዩ.ኤስ. አሜሪካ ብሔራዊ የሕዝብ ብዛት እድገት ኮሚሽን ሊቀመንበር በ1978 ዓ.ም. እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ጆን ዲ. ሮክፌለር ሦስተኛው መሆኑን ስንሰማ ግራ እንጋባ ይሆናል:: ሮክፌለር የዓለም ሕዝብ ብዛትን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ተጨማሪ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ጥሪ ያስተላለፈበትን በ1974 ዓ.ም. በቡካሬስት የተካሄደውን የዓለም ሕዝብ ብዛት ጉባኤን መርቷል:: ሀብት ዳግም ክፍፍልን ማበረታታት አለብን ያለው ሮክፌለር፣ «ያላቸው» ሰዎች ቀሪዎቹ እስኪደርሱባቸው ድረስ የኑሮ ደረጃቸውን በበጎ ፈቃደኝነት ዝቅ ማድረግ አለባቸው በሚል ጥሪውን አስተላልፏል:: እርግጥ ነው፣ ሮክፌለር ለሕዝብ ብዛት ምርምርና ቅነሳ የሚውል የሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር ለግሷል:: ይሁንና፣ የሮክፌለር



Scanned with CamScanner

ቤተሰብ ያቀረበውን ሀብትን የማካፈል ሐሳቡን ተግባራዊ ሲያደርገው አልተስተዋለም:: የውስጠ-ዐወቆቹ እስትራቴጂ፣ «ከልክ ያለፈ የሕዝብ ብዛት ድኽነትን ይፈጥራል:: ለዚህም መፍትሔው አዲስ የኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ነው» የሚል ነው:: ይህ አባባል አዲስ የዓለም ቋይስሆፕት ካስቀመጠው እምብዛም የተለየ አይደለም::

የኃይል እጥረት ሌላኛው ትልቅ ችግራችን ነው:: ይህን በሚመለከት ጥብቅ እርምጃ ካልወሰድን በስተቀር በጥቂት ዓመታት ውስጥ ኢንዱስትሪዎች መሥራት ያቆማሉ፣ ብርሃን የምናገኘው ከሻማ ይሆናል፣ እንዲሁም ወደ ሥራ ቦታችን የምንመላለሰው በቢስክሌት ይሆናል:: ታዲያ፣ ምን ማድረግ ሊኖርብን ነው? በቀዳሚነት ምቾትና ድሎት ወዳድ አሜሪካውያን ዐረቦቹ እየቆጠቡ የሚሰጡትን የዓለማችንን ቀሪ ውድ ነዳጅ ዘይት አጠቃቀማቸውን ገደብ እንዲያበጁለት ማድረግ አለብን:: በቀጣይነትም የኃይል ቀውስን ለመፍታት አንድ ዓለም-አቀፋዊ ድርጅት መመሥረት ይኖርብናል::

መቼም፣ እነኝህን ሁሉ አድርገናል:: የዓለም ኤነርጂ ኮንፈረንስ ዓለም-አቀፍ ኤነርጂ ኤጀንሲ ተቋቁሟል:: ይሁንና፣ ከ1973 ዓ.ም በፊት ስለ የኃይል እጥረት ችግር አለመስማታችን የሚገርም ነው በዚህን ወቅት ነዳጅ ዘይት ርካሽና የተትረፈረፈ ነበር:: የዮም ኪፑር (የ17ቱ ቀን) ጦርነትና የዐረቦች የነዳጅ ዘይት ማዕቀብ ሲፈጠሩ ግን የነዳጅ ዘይት ዋጋ ጣሪያ ነካ::

ይህን ጊዜ ዐረቦቹ በቢሊዮን የሚቆጠር ዶላር ያፍሱ ጀመር ዶላሩን የዛቁት ግን እነሱ ብቻ አይደሉም:: ነዳጅ ዘይት የሚያጣሩትና የሚነግዱት ኩባንያዎች ከአጠቃላይ ትርፉ 33% ኪሳቸው ውስጥ ያስገባሉ::

ኤክሶን «የነዳጅ ዘይት የተባበሩት መንግሥታት» የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል:: ይኸው ኩባንያ ከ300 በላይ በሆኑ ቅርንጫፎቹ ወኪሎቹ አማካኝነት ቢያንስ ለ100 ሀገራት ነዳጅ ዘይት ያቀርባል::

በ1974 ዓ.ም. ኤክሶን ኮርፖሬሽን የዓለማችን ትልቁ ኢንዱስትሪያዊ ኮርፖሬሽን ሆኗል:: ከአንድ ዓመት በፊት ያገኘው የ$2.4 ቢሊዮን ትርፍ አንድ ኢንዱስትሪያዊ ኩባንያ ካስመዘገበው ትልቁ ነው:: የነዳጅ ዘይት ቀውስ የተፈጠረበት ዓመት ኤክሰንም

ሆነ የኩባንያው ዋነኛ ባለአክሲዮኖች ሮክፌለሮችን ቅንጣት ታህል አልጎዳቸውም::

ዩ.ኤስ አሜሪካ በበኩሏ የራሷን የነዳጅ ዘይት ክምችት አምቃ እንደያዘች ነው:: ወደ ትክክለኛው የሚቃረቡ ግምቶች ዩ.ኤስ. አሜሪካ በአለት ውስጥ ከሚገኘው ነዳጅ ዘይት ውጭ በመቶ ቢሊዮን የሚቆጠር በርሜል እንዳላት ያስቀምጣሉ:: የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት እንደሚለው፣ በዩ.ኤስ. አሜሪካ በአለት ውስጥ የሚወጣ 80 ቢሊዮን በርሜል ነዳጅ ዘይት ሲኖራት፣ በተሻሻለ ቴክኖሎጂም 600 ቢሊዮን በርሜል ማውጣት ትችላለች::

አሜሪካ በዙሪያዋ ባሉት ባሕሮች 780 ቢሊዮን በርሜል የሚገመት ነዳጅ ዘይት ያላት ሲሆን፣ በአላስካም ሌላ 20 ቢሊዮን በርሜል አላት:: በዚህም መሠረት፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ በ1480 ቢሊዮን በርሜል ነዳጅ ዘይት ላይ ተቀምጣለች ማለት ነው:: ሀገሪቷ በዓመት የምትጠቀመው ደግሞ 6 ቢሊዮን በርሜል ነዳጅ ዘይት ብቻ ነው:: ያም ሆኖ፣ አሜሪካ በቅርቡ የኃይል እጥረት ያጋጥማታል ይባላል:: ይህን የሚሉት ውስጠ-ዐወቆቹና ለዓላማቸው ማስፈጸሚያነት የሚጠቀሙባቸው ወገኖች ናቸው::

ለችግሩ ተጠያቂ እየሆኑ ያሉት ደግሞ በአብዛኛው ዐረቦቹ ናቸው:: ጄራልድ ፎርድና ሄንሪ ኪሲንጀር የነዳጅ ዘይት ዋጋ ከተጭበረበረ ወይም ሌላ ማዕቀብ ከተጣለ ዩ.ኤስ. አሜሪካ መካከለኛውን ምሥራቅ ልትወር እንደምትችል በይፋ ተናግረዋል:: ይህ ዓይነቱ ቀውስና ሁኔታ «የነዳጅ ዘይት ምርት፣ ዋጋ አወጣጥና አከፋፈል ዓለም አቀፋዊነት» እንዲኖረው ያደርጋል:: ነዳጅ ዘይትን ሞኖፖል የያዘው ወገንም ዓለምን ይቆጣጠራል::

ለማንኛውም ዓይነት ችግር «መፍትሔ ሰጪ» ዓለም አቀፋዊ ድርጅት ተመሥርቶለታል:: ለምሳሌ ያህል፣ ለአደንዛዥ ዕፅ ችግር የተባበሩት መንግሥታት የአደንዛዥ ዕፅ አጠቃቀም ቁጥጥር ፈንድ፣ ዓለም አቀፍ ናርኮቲክስ ቁጥጥር ቦርድ፣ የናርኮቲክ መድኃኒቶች ዲ.ቪ.ዥን አሉ::

ከቀዬአቸው ለተፈናቀሉ ሰዎች የተባበሩት መንግሥታት ስደተኞች ኮሚሽን አለ:: ለችግረኛ ሕፃናት የተባበሩት መንግሥታት ሕፃናት



Scanned with CamScanner

ፈንድ አለ። ይህችን ዓለም ለተሰናበቷት ዓለም አቀፍ የሞት ዲክላሬሽን ቢሮ አለ። በሽታን ለመዋጋት የዓለም ጤና ድርጅት አለ። አዲስ ዓይን ካስፈለገን፤ ዓለም አቀፍ የዓይን ባንክ አለ። ለማኅበረሰቡ ግማሽ አካል ዓለም አቀፍ የሴቶች ካውንስል አለ። በረራን በሚመለከት ዓለም አቀፍ ሲቪል አቪዬሽን ድርጅት አለ። ሀገራት ገንዘብ መበደር ከፈለጉ የዓለም ገንዘብ ድርጅት (አይ.ኤም.ኤፍ.) እና የዓለም ባንክ አሉ። በአሁኑ ዘመን «ዓለም አቀፍ» ያልተባለለት ነገር ያለ አይመስልም።



Scanned with CamScanner

ምዕራፍ 13

# ኤስ.ዲ.አር.

«ለስንፍና መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ፤ ደስ የሚለውም ቢኖር እርሱ ይዘምር።»

(የያዕቆብ መልእክት 5:13)

ፋይናንስን በሚመለከት ዓለማችን «የገንዘብ ቀውስ» ከተባለ ዘርፈ ብዙ ችግር ጋር ተፋጥጣለች። በዚህም ምክንያት ከፋይናንስ ጋር ተያያዥነት ያለውን ለውጥ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብን እየተነገረን ነው። ለለውጡ አስፈላጊነት ከሚሰጡ ምክንያቶች መካከል ቀጣዮቹን እናገኛለን።

1. የዋጋ ግሽበት፡- ለተራው ሕዝብ የዋጋ ግሽበት የኑሮ ውድነት መጨመር ማለት ነው፤ ለችግሩ ተጠያቂ የሚደረጉትም ከፍተኛ ደመወዝ እንዲከፈላቸው የሚጠይቁ ሠራተኞችና የመሠረታዊ ሸቀጦችን ዋጋ እንዳሻቸው የሚጨምሩ የጥሬ እቃ አምራቾች ናቸው። በእርግጥ፣ ለችግሩ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ነገሮች አሉ። ይሁንና፣ ዋነኛው የዋጋ ግሽበት መንሥዔ የገንዘብ አቅርቦት መጨመር ነው። የገንዘብ አቅርቦትን የመጨመርም ሆነ የመቀነስ ሥልጣን ያለው ደግሞ የፋይናንስ ሥርዓቱን በሚቆጣጠሩት ሰዎች ዘንድ ነው። «ተጨማሪ የገንዘብ ኖት ማተሙ» ጥሩ ሐሳብ ሊመስል ይችላል። የወረቀት ገንዘብ ግን እውነተኛ ገንዘብ አይደለም፤ እንደ የተስፋ ሰነድ ልንወስደው እንችላለን። ተጨማሪ የገንዘብ ኖት በሰው እጅ ሲገባ ደግሞ፣ የእውነተኛው ሀብት (ሸቀጥ) ዋጋ ከፍ ስለሚል የወረቀት ገንዘቡ ዋጋ ይቀንሳል።
በአሁኑ ወቅት አውሮጳ ውስጥ አንድ ሁለት ሰዎች ምግብ ቤት ገብተው ለተስናገዱበት $1000 መክፈላቸው እየተለመደ መጥቷል። ይህም የሆነበት ምክንያት ከበፊቱ የበለጠ የገንዘብ ኖት መዘዋወሩ ነው። ከዛሬ 50 ዓመት በፊት የ$100 ደመወዝተኛ በአሁኑ ዘመን $1000 በወር ከሚያገኘው ሠራተኛ የተሻለ ሕይወት ይኖር ስለነበር

የሕዝቡ ገቢ ቢጨምርም ሀብታም ሆኗል ማለት አንችልም:: ይኸው ሁኔታ አካባቢያዊ ብቻ ሳይሆን ዓለም አቀፋዊም ችግር ነው:: ሀገራትን ለሚቆጣጠሩ አካላት ተጨማሪ ትርፍ ማስገኛና የቁጥጥር መረባቸው ማጠናከሪያ ዘዴ ነው::

በአንድ ወቅት ብሔራዊ የፋይናንስ እስትራቴጂ ቢሆንም፣ በአሁኑ ጊዜ ዓለም አቀፋዊ መልክ ይዟል:: የዋጋ ግሽበትም የማኅበረሰብን ውድቀት የሚያፋጥን ችግር ተደርጎ ተጋንኖ ቀርቧል:: ለአንድ ዳቦ $100 የመክፈል ስጋት ተራውን ሕዝብ እንደሚያሸብር ምንም ጥርጥር የለውም:: በዛሬው ዘመን እንኳን ተራው ሕዝብ፣ «የኑሮ ውድነት የት ሊደርስ ነው?» እያለ በማለቃቀስ ላይ ነው:: ችግሩን የሚፈቱለት ጥሩ፣ ሐቀኛና ራስ ወዳድ ያልሆኑ መሪዎች እንዲኖሩ ተስፋ ያደርጋል::

2. <u>የዓለም ንግድ</u>፡- በ1973 ዓ.ም. ወደ .$367 ቢሊዮን ያደገው የዓለም ንግድ በአሁኑ ወቅት የት እንደደረሰ መገመቱ ብዙም አይከብድም:: ከዓለም ንግድ ጋር ተያያዥነት ካላቸው ችግሮች መካከል አንዱ የተለያዩ ሀገራት ገንዘብ ዋጋ ተለዋዋጭነት ነው:: የተወሰኑ ሀገራት ገንዘብ ዋጋ በየቀኑ ሊለዋወጥ ይችላል:: በእርግጥ፣ መንግሥታት የገንዘባቸውን ዋጋ የመቀነስ ወይም የመጨመር ምርጫቸው በሂደቱ አጉል ቦታ ያሉትን ኩባንያዎች ውድቀት፣ እንዲሁም «ባወጣ ያውጣው» መርሕ ላይ የተመሠረተ ኢንቬስትመንት ማስከተሉ አይቀርም::

የገንዘብ ዋጋ እንዲዋዥቅ የሚያደርጉትን አካላት ማንነት መጥቀስ ለቀባሪው አረዱት ዓይነት ይሆናል:: እነኝህ አካላት ሀገራት እስከ አፍ ገደፋቸው ጦር መሣሪያ እንዲታጠቁ ካበረታቱ በኋላ እንዲጠቀሙበት በመገፋፋት ተጨማሪ ጦር መሣሪያ እንዲገዟቸው ሁኔታዎችን የሚያመቻቹ ናቸው::

3. <u>የፋይናንስ ሥርዓቱ ዘገምተኛነት</u>፡- ቼኮችን የሚጠቀመው የፋይናንስ ሥርዓት በበርካታ መልኩ አመቺ ነው:: ሊሰረቅ የሚችል ሻንጣ ሙሉ ገንዘብ ይዞ ከመዘዋወርም ቼክ መጠቀሙ የተሻለ ነው:: ችግሩ ግን ቼክ አንዳንድ ጊዜ እስኪጣራ ድረስ ጥቂት ሳምንታትን መውሰዱና ጊዜ ማቃጠሉ ነው:: ምንም እንኳን ለብዙ ሰዎች የሥራ ዕድል



Scanned with CamScanner

ቢፈጥርም፣ ሥርዓቱ ጊዜው እያለፈበት ነው:: ስለዚህም፣ ከዚህ የፈጠነ ሥርዓት መዘርጋት ሊኖርብን ነው::

ለምሳሌ፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ በዓመት ከ30 ቢሊዮን በላይ ቼኮችን ታዘዋውራለች:: የአሜሪካ ባንክ ፕሬዚዳንት ራስል ፌንዊክ ከአንድ ሬዲዮ ጣቢያ ጋር ባደረጉት ቃለ-ምልልስ ላይ፣ «በአፋጣኝ አንድ ነገር መደረግ አለበት:: በወረቀት ክምር ውስጥ እየተዋጥን ነው:: በዚህ መልኩ ለረዥም ጊዜ መቀጠል አንችልም» ሲል ተናግረዋል:: በሌላ አነጋገር፣ ችግሩ መፍትሔ ያሻዋል::

አዲሱ የፋይናንስ ሥርዓት ለዓለም መንግሥት አስፈላጊ ነው:: የዎተርጌት ቴፕ ክሮች እንዳጋለጡት፣ ሪቻርድ ኤም. ኒክሰን ዩ.ኤስ. አሜሪካ የነጻውን ዓለም ገንዘብ ለማረጋጋት የማትሞክረው አዲስ የፋይናንስ ሥርዓት ለመዘርጋት ስላቀደች እንደሆነ ተናግረዋል:: የፋይናንስ ቀውሱን እንዲፈቱ የተቋቋሙት ድርጅቶች ዓለም ባንክና የዓለም ገንዘብ ድርጅት (አይ.ኤም.ኤፍ.) ናቸው::

## የዓለም ባንክ እና የዓለም ገንዘብ ድርጅት (አይ.ኤም.ኤፍ.)

ሁለቱም ድርጅቶች የሚሠሩት በተባበሩት መንግሥታት መዋቅር ውስጥ ነው:: እርግጥ ነው፣ ሁለቱ ባንኮች በ1948 ዓ.ም. እንዲቋቋሙ ትልቁን ሚና የተጫወቱት ዓለም አቀፍ ባንከኞች ናቸው:: ሁለቱም ተቋማት ከእያንዳንዱ አባል ሀገር የተወከሉ አንዳንድ ሰዎች ያሉበት የገዢዎች ቦርድና 18 ዳይሬክተሮች (6+6+6) የያዘ ሥራ አስፈጻሚ አላቸው::

አይ.ኤም.ኤፍ. መጋቢት 31/1969 ዓ.ም. በስተመጨረሻ ላይ ወርቅንም ጨምሮ ሁሉንም የገንዘብ ዓይነቶች የሚተካ አዲስ ዓይነት የገንዘብ ምንዛሬ እንደሚጀምር ይፋ ሲያደርግ የዓለማችን ሕዝብ ስለ መጪው የፋይናንስ ሥርዓት መጠነኛ ግንዛቤ አግኝቷል:: ይህ አዲስ ዘዴ «የወረቀት ወርቅ» የሚል መጠሪያ ቢሰጠውም፣ በውኑ ወረቀትም ሆነ ወርቅ አይደለም:: ኤስ.ዲ.አር. (*ስፔሻል ድሮዊንግ ራይትስ*) የተሰኘ የቁጥር/ብድር ሥርዓት ነው::

ይኸው አዲስ ሥርዓት ይፋ በሆነበት ቀን ፖል ሽዌይትዘር፣ «ክቡራትና ክቡራን፣ በትክክለኛው ጊዜ ላይ ነን» ሲል ተናግሯል::



Scanned with CamScanner

በ1976 ዓ.ም. አይ.ኤም.ኤፍ. ወርቅ የድርጅቱ መጠባበቂያ መሆኑ ቀርቶ በኤስ.ዲ.አር. እንደሚተካ አስታውቋል። ከዚህን ጊዜ ወዲህ ተቋሙ የወርቅ ይዞታውን በጨረታ እየሸጠ ነው።

ኤስ.ዲ.አር. የእያንዳንዱን አባል ሀገር ብድር የሚወክል በዓለም አቀፍ «የሒሳብ መዛግብት» ውስጥ ያለ ቁጥር ነው። ኤስ.ዲ.አር. በአሁኑ ወቅት ለዓለም አቀፍ ንግድ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው። ምንም ዓይነት የገንዘብ ኖት ጥቅም ላይ የማይውል ሲሆን፣ ሀገራቱ በሚፈጽሙት ግዢ ወይም ሽያጭ ሒሳባቸው ውስጥ ይገባላቸዋል ወይም ይቀነስባቸዋል። ኤስ.ዲ.አር. አሁን ካሉት የገንዘብ ኖቶች ጋር በተገናኘ ዋጋ አለው። ለምሳሌ ያህል፣ አንድ ኤስ.ዲ.አር. በአይ.ኤም.ኤፍ. ሒሳብ መዝገብ $1.20 ነው።

ይሁን እንጂ፤ በስተመጨረሻ ላይ ሁሉም የገንዘብ ኖቶች ጊዜው ያልፍባቸውና ይሰረዛሉ። ይህን ጊዜ ኤስ.ዲ.አር. ለሀገራት ብቻ ሳይሆን ለግለሰቦችም ጭምር ብቸኛው የመገበያያ ዘዴ ይሆናል። ትላልቆቹ ሀገራት ሥርዓቱን ተግባራዊ ካደረጉ ሁሉም ሀገራት ይህንኑ ፈለግ መከተላቸው አይቀርም። ለዚህ አካሄድ ብቸኛው አማራጭ ከዓለም ንግድ ሙሉ በሙሉ መገለል ነው።

ወደ ኤስ.ዲ.አር. የሚደረገው ሽግግር በበርካታ አካባቢዎች እየታየ ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ከ1977 ዓ.ም. ወዲህ የተለያዩ አየር መንገዶች የመንገደኛና የጭነት ክፍያን በኤስ.ዲ.አር. እያስሉ ነው። በኦፔክ ሥር የታቀፉ ነዳጅ ዘይት አምራች ሀገራት የአከፋፈል ሥርዓቱ በኤስ.ዲ.አር. ላይ ለማድረግ እያሰቡበት ነው።

ኤስ.ዲ.አር. የሚያስፈልገው መላው ዓለም አንድ «የገንዘብ ኖት» እንዲጠቀም ብቻ ሳይሆን ጥሬ ገንዘብ ከመስጠት ይልቅ ክፍያን እዚያው በዚያው ለመፈጸም ጭምር ነው። በእርግጥ፣ ኤስ.ዲ.አር. ቁጥር በመሆኑ «ለሌላኛው ወገን ሊሰጥ» አይችልም፤ ቁጥሩ በሒሳብ መዝገብ ውስጥ ይገባል ወይም ይቀነሳል እንጂ። የሒሳብ መዝገቡ ደግሞ በወረቀት የሚዘጋጅ ሳይሆን ኮምፒዩተር ነው።

ኮምፒዩተር ከሰው ልጅ በብዙ እጥፍ ፍጥነት መሥራት ይችላል። አንዳንድ የዘመናችን ኮምፒዩተሮች ደግሞ በአንድ የሕዝብ ቤተ-



Scanned with CamScanner

መጻሕፍት ውስጥ ካለው የበለጠ መረጃ መያዝ ይችላሉ:: በኮምፒዩተር መስክ ምን ያህል እንደተጓዝን ለማሳየት ያህል የየካቲት 1976 ዓ.ም. ኮምፒዩተር ዳይጀስት መጽሔት እትም ያሰፈረውን እንመልከት:: «የዛሬ ዘመን ኮምፒዩተር የተደፋ አንድ ሲኒ ቡና ከጠረጴዛው እስከ ወለሉ ለመድረስ በሚፈጅበት ግማሽ ሴኮንድ ውስጥ ቀጣዮቹን ሥራዎች ማከናወን ይችላል::

- 2000 ቼኮችን በ300 የተለያዩ የባንክ ሒሳቦች ያስገባል፤
- የ1000 ሕሙማንን የልብ ምርመራ ያካሂዳል፤
- ጥያቄዎቹን እየመረመረ በ3000 ፈተናዎች በአንድ ጊዜ 150000 መልሶችን ያርማል፤
- 1000 ሠራተኞች ያሉትን ኩባንያ የደመወዝ ክፍያ አሰልቶ ያቀርባል::

«አንድ ኮምፒዩተር 5000 ጫማ ርዝመት ባለው አንድ የቴፕ ክር ላይ የ220 ሚሊዮን አሜሪካውያንን ስም፣ አድራሻ፣ የባንክ ሒሳብና ሌሎች የግል መረጃዎችን መመዝገብ ይችላል::»

ኮምፒዩተሮች በአሁኑ ዘመን በብዛት እየተመረቱ ሲሆን፣ አብዛኞቹ ኩባንያዎችም የራሳቸው ማሺን አላቸው:: (እንደ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮና አስፈላጊ የቤት እቃም እየሆነ መጥቷል::) ይሁን እንጂ፣ አንዳንድ ኩባንያዎች በየወሩ ቢበዛ ለአምስት ቀናት ብቻ ኮምፒዩተሮችን በመከራየት የሚፈልጉትን ሥራ ያከናውኑበታል::

አዲሱ የገንዘብ ሥርዓት ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ እንዲውል ቀጣዮቹ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው::

1. ሁሉም የሸቀጥ ዓይነት በኮምፒዩተር የሚታወቅ መለያ ምልክት ሊኖረው ይገባል:: ይህም በአሁኑ ወቅት ከምዕራቡ ዓለም ባለፈ በሌሎች ሀገራትም ተግባራዊ እየሆነ ነው:: የክብሪት ፓኮ ሳይቀር እያንዳንዱ እቃ ከእስክሪብቶ በማይትልቅ አነስተኛ ኮምፒውተር የሚነበብና የሚመዘገብ መሥመሮችንና ቁጥሮችን ያካተተ ምልክት እየተደረገበት ነው::
2. ማንኛውም ግብይት በኮምፒዩተር አማካኝነት መካሄድ አለበት:: ይህም አሠራር በተለያዩ ሀገራት ተግባራዊ እየሆነ ነው::



Scanned with CamScanner

3. ኤስ.ዲ.አር. ቼክንና ጥሬ ገንዘብን በመተካት መደበኛ የመገበያያ ዘዴ መሆን አለበት:: ይህም በዓለም አቀፉ መድረክ እየተሠራበት ነው::
4. እያንዳንዱ ግለሰብ በብሔራዊ ኮምፒዩተር ሥርዓት የሒሳብ ቁጥሩ የሚሆን የግል ቁጥር ሊሰጠው ይገባል::
5. ቁጥሩ እንዳይረሳ ወይም እንዳይጠፋ፣ እንዲሁም አጭበርባሪነትን ለማጥፋት ሲባል በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ መነቀስ አለበት::

በመላው አሜሪካ በሚገኙ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች በስፋት የሚሰራጭ አንድ መጽሔት አዲሱ ሥርዓት ምን እንደሚመስል በግልጽ አስቀምጦታል:: «ማንኛውም ግዢና ሽያጭ የሚፈጸመው በኮምፒዩተር አማካኝነት ይሆናል:: የገንዘብ ኖት፣ ሳንቲም ወይም ቼክ ጥቅም የላቸውም:: በመርሃ ግብሩ ሰዎች የተሰጣቸውን ቁጥር በእጃቸው ወይም ግንባራቸው ላይ ይነቀሱታል:: ቁጥሩ ቆዳ ላይ እንዲያርፍ የሚደረገው በሌዘር ጨረር ስለሆነ ምንም ዓይነት ስሜት አይፈጥርም:: ቁጥሩ በዓይናችን ልናየው የማንችል ሲሆን፣ እንደ ጣት አሻራ ቋሚ ነው:: እያንዳንዱ ሸቀጥ የኮምፒዩተር ምልክት ይሰጠዋል:: በየመደብሩ ያለው የሸቀጦቹን መለያ ቁጥር የሚመዘግበው ኮምፒዩተር በግለሰቡ ሰውነት ላይ ያለውን ቁጥር በመመዝገብ ከኤስ.ዲ.አር. ሒሳቡ ላይ የገዛውን ሸቀጥ ዋጋ ይቀንሳል::»

አንዳንድ ሰዎች፣ «ምንም የሚያሳስብ ነገር የለም:: ይህን ዓይነቱን ሥርዓት ለመዘርጋት ብዙ ዓመታት ይፈጅባቸዋል» ይሉ ይሆናል:: ዳሩ ግን፣ የሌዘር ጨረር ገና ከወዲሁ ከብትና ሳልሞን ዓሣ ላይ ምልክት ለማድረግ ጥቅም ላይ እየዋለ ነው:: ዓሣው ምልክት የሚደረግበት እየዋኘ እያለም ሊሆን ይችላል:: የሰው ልጅን ለዓይን የማይታይ ቁጥር ለመንቀስ የሚያገለግለው የሌዘር ጨረር ተዘጋጅቷል:: ጨረሩ ምንም ዓይነት የሕመም ስሜት ሳይፈጥር የቆዳውን ቀለም በማጥፋት ለዓይን የማይታይ ቁጥር በግለሰቡ ላይ ያሳርፋል::

የአይ.ኤም.ኤፍ. እቅድ እያንዳንዱን ሰው 18 ቁጥሮችን (6+6+6) በያዘ አኃዝ መንቀስ ነው:: ቁጥሩ የግለሰቡን የባንክ ሒሳብ ብቻ ሳይሆን ትውልድ፣ ዜግነት፣ ሃይማኖት፣ የሥራና የትምህርት ደረጃ

መሰሉ የግል መረጃዎችን ጭምር ወደ ኮምፒዩተሩ የሚያስተላልፍ
ው፡፡ የእያንዳንዱ ግለሰብ ማንነት በእጁ ወይም በግምባሩ ላይ
ስፈር እንዳለበት የሚገልጹ የባንክ ፎርሞች ታትመው
ዘጋጀታቸው ይታወቃል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ለዓይን
ማይታየው ቁጥር በእጁ ላይ ከተነቀሰ አንድ ውስጠ-ዐወቅ ጋር
ገናኝቷል፡፡

የዓለምን ንግድ በኮምፒዩተር ለመመዝገብ የተሠሩትና «አውሬው»
ሚል መጠሪያ የሚታወቁ በብራስልስና ሉክሰምበርግ የሚገኙ ትላልቅ
ምፒዩተሮች እንዳሉ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን ተዘግቧል፡፡ እነኝህ
ባዎች «የፈጠራ ሥራ ናቸው» በሚል ተፈርጀዋል፡፡ የአውሮጳ
ኅበረሰብ ዋና ጽሕፈት ቤትም «አውሬው» የሚባል ኮምፒዩተር አለ
ባሉን አስተባብሏል፡፡

መካድ የማይቻለው ኮምፒዩተሮቹ የንግድ ሥርዓታችን አካል
ሆናቸውንና ያለነሱ መሥራት እንደማንችል ነው፡፡ በመላው ዓለም
ያ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ትላልቅ የኮምፒዩተር ማእከላት ያሉ
ያን፣ እነኝህም እርስ በርስ እንዲገናኙ እየተደረገ ነው፡፡ እነኝህ
ከላት መካከል አንዱ ዩሮኔት ነው፡፡ ሥርዓቱን ለማፋጠን ትልቁን
ና እየተጫወቱ ካሉት ነገሮች መካከል አንዱ ኢንተርኔት ነው፡፡
ተር ኪሲንጀር እንዳሉት፣ የእርስ በርስ መደጋገፋችንን የማፋጠን
ር አለብን፡፡

አዲሱ የፋይናንስ ሥርዓት የተባበሩት መንግሥታት እያራመደው
ው አዲስ ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት አካል ነው፡፡ (አንድም
፡ ይህን በሚመለከት ተቃውሞውን ሲያሰማ አልተደመጠም፡፡)
ባበሩት መንግሥታት ግንቦት 2/1974 ዓ.ም. ባቋቋመው አዲስ
ም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት የመመሥረቻ ጽሑፍ መግቢያ
፡ «እኛ፣ የተባበሩት መንግሥታት አባል ሀገራት... በእኩልነት፣
ላዊ እኩልነት... ላይ ለተመሠረተ አዲስ ዓለም አቀፍ ኢኮኖሚያዊ
ዓት ምሥረታ ባስቸኳይ ለመሥራት በጋራ ቆርጠን መነሣታችንን
ለጻለን» ብሏል፡፡

ከ1974 ዓ.ም. ወዲህ ይህን አዲስ ኢኮኖሚያዊ ሥርዓት ለመገንባት
ም አቀፋዊ ግፊት እየተደረገ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የአጋጣሚ



Scanned with CamScanner

ጉዳይ የማይመስሉ ጥቂት አስገራሚ እውነታዎች እየተከሰቱ ነው።
ለምሳሌ፣ በሊር ሲግል ኩባንያ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ውስጥ ተመርተው ወደ
እስራኤል የሚላኩ ኮምፒዩተሮች እያንዳንዳቸው 666 ቁጥር
ያረፈባቸው ናቸው:: የታወቁት ሰባኪዎች ዶክተር ጃክ ቫን ኢምፔ
ሆዋርድ ኤስቴፕ ለኅትመት ባበቋቸው ሥራዎቻቸው ለሸቀጣ ሸቀጥ
ማከማቻና ሽያጭ የተዘጋጀው አዲሱ የኮምፒዩተር ሥርዓት 666
ቁጥር የያዘ መለያ ኮድ እንዳለው መረጃ የደረሳቸው መሆኑን
ገልጸዋል::

በእርግጥ፣ አዲሱ ሥርዓት በርካታ ጥቅሞች አሉት:: ኮምፒዩተሩን
መስረቅ የፈለጉ ወሮበሎች ከሌሉ በስተቀር የሚሰረቅ ገንዘብ
ስለማይኖር የባንክ ዘረፋ ያበቃል:: ግብይት ወዲያውኑ ባንዳፍ
ይካሄዳል:: ገንዘብ አይጠፋም:: (አንዳንዶች የመጨረሻዎቹ ሁለት
ነጥቦች ላይዋጡላቸው ይችላሉ::)

የሥርዓቱ አደጋ ያለው «ማን ይቆጣጠረዋል?» ከሚለው ጥያቄ
ጋር በተያያዘ ነው:: የሚቆጣጠረው ሰው 666 ቢሆንስ? ማብሪያ
ማጥፊያው ያለው በኃይል 13 እጅ ቢሆንስ?

በዮሐንስ ራእይ የተቀመጠው ትንቢት የክርስቶስ ተቃዋሚ
መላውን ዓለም እንደሚገዛ፣ እያንዳንዱ ሰው በግንባሩ ወይም ቀኝ እጁ
ላይ መለያ ምልክቱን እንደሚቀበል፣ አገልግሎት ጨምሮ ማንኛውም
ግዢና ሽያጭ በቁጥጥሩ ሥር እንደሚሆን በግልጽ አሳይቷል።
ቢልደርበርገሮች በከፊል ያቆሙት አዲሱ የፋይናንስ ሥርዓት
የአውሬው፣ ማለትም ሰው 666፣ የራሱ ሥርዓት ሊሆን ይችላል።
አንድ ነገር በእርግጠኛነት ማስቀመጥ ግን ይቻላል:: የአውሬው
የመለያ ምልክት አሠራር ተግባራዊ ሲሆን ከአምልኮተ-ሰይጣን
ለሰይጣን ከሚኖር ታማኝነት ጋር የሚዛመድ ይሆናል::

ኤስ.ዲ.አር. ለሚጠቀመው አዲሱ ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት ዋስት
የሚሰጠው ማን ነው? የሚል ጥያቄ መነሣቱ የማይቀር ነው:: ሁሉ
ሀገራት ዕዳ ስላለባቸው አንድ መንግሥት ወይም የተሰ
መንግሥታትን ያቀፈ ቡድን ሊሆን አይችልም:: ዋስትና መስ
የሚችሉት ሀገራቱን በመዳፋቸው ውስጥ ያስገቡት ዓለም አ
ባንከኞች ብቻ ናቸው::



Scanned with CamScanner

ለአሜሪካ ዶላር ዋስትና የሚሰጠው ማን ነው? ዋስትና የሚሰጠው ባል ይዞታ ሥር ባሉ ዓለም አቀፍ ባንኮች ቁጥጥር ሥር ያለው ፌደራል ሪዘርቭ ሥርዓት ነው:: ለኤስ.ዲ.አር. ዋስትና መስጠት ሚችሉ እነኝህ ወገኖች ናቸው:: ምክንያቱም ዓለም በመዳፋቸው ሥር ትና::

የሰው ልጅ ሰብእና ውድ ዋጋ ተከፍሎበታል:: ይህም ዋጋ ተከፈለው በወርቅ፣ በወረቀት ገንዘብና በወታደሮቹ ደምና አጥንት ው:: ያም ሆኖ፣ ኃይል 13 ገዝቶታል:: በዚህ ረገድ ጥርጣሬ ደረብን፣ (ሌዘር ጨረሩን በመጠቀም?) ሕዝቡን በ666 ማኅተም ልክት በማድረግ ያረጋግጥልናል::

ይሁንና፣ ሁሉም የሰው ልጅ ለሰይጣን ያደረ አይደለም:: ክርስቶስ ውድ ደም የዳኑና የተገዙ ስፍር ቁጥር የሌላቸው እግዚአብሔር ያደሩ ሰዎች አሉ::

«ከአባቶቻችሁ ከወረሳችሁት ከከንቱ ኑሮአችሁ በሚያልፍ ነገር ብር ወይም በወርቅ ሳይሆን፣ ነውርና እድፍ እንደ ሌለው እንደ በግ ም በክቡር የክርስቶስ ደም እንደ ተዋጃችሁ ታውቃላችሁ::» ጴጥሮስ መልእክት 1:: 1: 18-19)

እግዚአብሔር ሕዝቡ በእውነት የእሱ እንደሆነ ለማረጋገጥ በሁሉም ማኞች ላይ የራሱን ማኅተም ያሳርፍባቸዋል:: «እናንተም ደግሞ እውነትን ቃል፣ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፣ ሰምታችሁ ግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፣ በተስፋ መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ ትማችሁ፤ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፣ ለእግዚአብሔር ለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ፣ ይህም ለክብሩ ምስጋና ይሆናል:: (ወደ ፌሶን ሰዎች 1: 13-14)



Scanned with CamScanner

# ምዕራፍ 14

# አውሮጳ

**«በምድር ላይ ተቀማጥላችኋል በሴሰኛነትም ኖራችኋል፤ ለእርድ ቀን እንደሚያወፍር ልባችሁን አወፍራችኋል።»**

(የያዕቆብ መልእክት 5:5)

በዘመናችን ካየናቸው ዓበይት ድርጊቶች መካከል አንዱ በአንድ ወቅት ሮም ተብሎ ይጠራ በነበረው የዓለም ክፍል አንድ ትልቅ የሀገራት ፌደሬሽን ምሥረታ ነው። ቀደም ሲል የጋራ ገበያ ተብሎ ይጠራ የነበረውና በአሁኑ ወቅት የአውሮጳ ማኅበረሰብ በሚል የሚታወቀው የአውሮጳ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ማንኛውንም የውጭ ስጋት ለመቋቋምና በዓለማችን የመሪነትን ቦታ ዳግም ለማግኘት ሲባል ምዕራባዊ አውሮጳን ለማዋሐድ የሚደረግ ትልቅ ጥረት ነው።

በአሁኑ ወቅት አውሮጳ ውስጥ እየተካሄደ ያለው ነገር እንዲሁ በአጋጣሚ የተፈጠረ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንድ ትልቅ የሮም/አውሮጳ ኮንፌዴሬሽን እንደሚመሠረት ትንቢት አለ። ይህ ኮንፌዴሬሽን ውስጠ-ዐወቆቹ በመጨዎቹ ጥቂት ዓመታት ሊያጠናክሩት የሚተጉት ከምሥጢረ 666 ጋር የተቆራኘ ኅብረት ነው።

የታላቁን ናቡከደነፆር ሕልማዊ ምስልን ሰፋ አድርገን እንመልከት። ሁሉም ሕልሞች ትርጉም ያዘሉ ባይሆኑም፣ ዳንኤል ሕልሙንና ትርጉሙን በግልጽ ነግሮናል። ሕልሙ ስለ አራት ትላልቅ ግዛተ-አፄዎች፣ እንዲሁም ክርስቶስ ወደ ምድር ከመምጣቱ ቀደም ባሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ ስለሚፈጸመው የዓለም አገዛዝ ጥሩ ዕይታ ይሰጠናል። በቀዳሚነት ሕልሙ ምን እንደሚል እንመልከት።

«አንተ፣ ንጉሥ ሆይ፣ ታላቅ ምስል አየህ፤ ይህም ምስል ታላቅና ብልጭልጭታው የበዛ ነበረ፣ በፊትህም ቆሞ ነበር፤ መልኩም ግሩም ሆኖና ወገቡም ናስ፣ ጭኖቹም ብረት፣ እግሮቹም እኩሌ ብረት

ሱም ሸክላ ነበረ። እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው ተፈንቅሎ
ትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየህ።
ን ጊዜም ብረቱና ሸክላው፣ ናሱና ብሩ ወርቁም በአንድነት
ጩ፣ በመከርም ጊዜ በአውድማ ላይ እንዳለ እብቅ ሆነ፤ ነፋስም
ሰደው፣ ቦታውም አልታወቀም፤ ምስሉንም የመታ ድንጋይ ታላቅ
ራ ሆነ ምድርንም ፈፅሞ ሞላ።» (ትንቢተ ዳንኤል 2:31-35)

በቀጣይነት ደግሞ ዳንኤል ለሕልሙ የሰጠውን ትርጉም
ምልከት።

ሕልሙ ይህ ነው፤ አሁንም ፍቺውን ከንጉሡ ፊት እንናገራለን።
ት፣ ንጉሥ ሆይ፣ የሰማይ አምላክ መንግሥትንና ኃይልን፣
ታትንና ክብርን የሰጠህ የነገሥታት ንጉሥ አንተ ነህ።
ቀመጡበትም ስፍራ ሁሉ የሰው ልጆችንና የምድር አራዊትን
ማይ ወፎችንም በእጅህ አሳልፎ ሰጥቶሃል፣ ለሁሉም ገዥ
ድርጎሃል፤ አንተ የወርቁ ራስ ነህ። ከአንተም በኋላ ከአንተ የሚያንስ
ሌ መንግሥት ይነሣል፤ ከዚያም በኋላ በምድር ሁሉ ላይ የሚገዛ ሌላ
ስተኛ የናስ መንግሥት ይነሣል። አራተኛውም መንግሥት ሁሉን
እንደሚቀጠቅጥና እንደሚያደቅቅ ብረት ይበረታል፤ እነዚህንም ሁሉ
እንደሚፈጭ ብረት ይቀጠቅጣል ይፈጭማል። እግሮቹና ጣቶቹም
ሉ ሸክላ እኩሉም ብረት ሆኖ እንዳየሁ፣ እንዲሁ የተከፋፈለ
መንግሥት ይሆናል፤ ብረቱም ከሸክላው ጋር ተደባልቆ እንዳየሁ
ብረት ብርታት ለእርሱ ይሆናል። የእሮግቹም ጣቶች እኩሉ ብረት
ሉም ሸክላ እንደ ነበሩ፣ እንዲሁ መንግሥቱ እኩሉ ብረቱ እኩሉ
ካማ ይሆናል። ብረቱም ከሸክላው ጋር ተደባልቆ እንዳየሁ፣ እንዲሁ
ው ዘር ጋር ይደባለቃሉ፤ ነገር ግን ብረት ከሸክላ ጋር
እንደማይጣበቅ፣ እንዲሁ እርስ በርሳቸው አይጣበቁም። በእነዚያም
ሥታት ዘመን የሰማይ አምላክ ለዘላለም የማይፈርስ መንግሥት
ሣል፤ ለሌላ ሕዝብም የማይሰጥ መንግሥት ይሆናል፤ እነዚያንም
መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፋቸውማለች፣ ለዘላለምም
ቆማለች። ድንጋዩም እጅ ሳይነካው ከተራራ ተፈንቅሎ ብረቱንና
ሱን ሸክላውንና ብሩን ወርቁንም ሲፈጨው እንዳየህ፣ እንዲሁ ከዚህ
ኋላ የሚሆነውን ታላቁ አምላክ ለንጉሡ አስታውቆታል፣ ሕልሙም
ውነተኛ ፍቺውም የታመነ ነው።» (ትንቢተ ዳንኤል 2:36-45)

## አራት የዓለም ግዛተ-አፄዎች

ምስሉ አራት የዓለም ግዛተ-አፄዎችን የሚወክል ነው:: በወርቅ ጭንቅላቱ የሚወከለው የመጀመሪያው ክፍል ታላቁ የናቡከደነፆር የባቢሎን ግዛተ-አፄ ነው:: ሰይጣን በዚህን ጊዜ 60x6 ክንድ የሆነ የወርቅ ምስል በማቆም የዓለም ሕዝብ እንዲያመልከው ሊያስገድደው ሞክሯል::

ከብር በተሠራው ደረቱና እጆቹ የሚወከለው ሁለተኛው ክፍል የፋርስ ግዛተ-አፄ ነው:: ይኸው ግዛተ-አፄ በንጉሥ ብልጣሶር ዘመን አገዛዝ የባቢሎንን ግዛተ-አፄ በመያዝ አጥፍቶታል::

ሦስተኛው በናስ አካሉ የሚወከለው የግሪክ ግዛተ-አፄ ነው::

በብረት እግሮቹ የሚወከለው አራተኛው ግዛተ-አፄ በጭካኔውና በጥንካሬው የሚታወቀው የሮማውያን ነው:: የሮማውያን ግዛተ-አፄ በዘመኑ የነበሩትን ሀገራት በሙሉ በማስገበር ከምድረ-ገጽ አጥፍቷቸዋል::

ከብረትና ከሸክላ የተሠሩት እግሮቹና ጣቶቹ የሮም ግዛተ-አፄን የመጨረሻ መልክ የሚወክሉ ናቸው:: ግዛተ-አፄው በዚህን ጊዜ ክርስቶስ ወደዚህች ምድር ዳግም ከመምጣቱ በፊት ባሉት ጥቂት ቀናት ውስጥ የሚስፋፉ በቀላሉ የሚፈርስ ጠንካራ ግዛት ነው::

የ10 ግዛተ-መንግሥታት ኮንፌዴሬሽን በርካታ ምዕተ-ዓመታት ያስቆጠረውን ምሥጢረ 666 ለማሟላት በመከራውና በሥቃዩ ዘመን የሚመጣው የክርስቶስ ተቃዋሚ (የሰይጣን ሰው) የሚመራ የአውሮጳ/የሮም ግዛተ-አፄ ነው:: ይህ ግዛተ-አፄ በሴራ፣ በማስገደድ፣ በፈቃደኝነትና በወረራ መላውን ዓለም በመቆጣጠሩ ቢሳካለትም፣ ዕድሜው ከጥቂት ዓመታት ያለፈ አይሆንም:: የሰይጣን የመጨረሻው የዓለም ግዛተ-አፄ «በድንጋዩ» ይጠፋል:: ድንጋዩ የሚወክለው ኢየሱስ ክርስቶስም በመላው ዓለም ግዛቱን ይመሠርታል::

ይኸው መከራ ሰይጣን አሁን ባለንበት ዘመን እያካሄደ ያለው የመጨረሻ ጥረቱ ነው:: ሰይጣንና ጋኔናዊና ሰብአዊ ግብረ-አበሮቹ አዲስ ዓለም አቀፋዊ ጋኔናዊ ሥርዓት በመላው ዓለም ለማስፈን እየሠሩ ነው:: ለበርካታ ምዕተ-ዓመታት ሲሠራ የቆየው እቅድ የአንድ ዓለም መንግሥት፣ የአንድ ዓለም የፋይናንስ ሥርዓትና የአንድ ዓለም

ሃይማኖት፣ ማለትም አምልኮተ-ሰይጣን፣ ማጠናከር የሚችል ኃያል የዓለም ገዢ ታሳቢ ያደረገ ነው::

የአውሮጳ የጋራ ገበያ የተመሠረተው ስድስት ሀገራት በ1957 ዓ.ም. ተሰባስበው የሮም ስምምነት ተብሎ የሚታወቅ ታሪካዊ ሰነድ እንደፈረሙ ነው:: ስድስቱ ሀገራት ጣልያን፣ ምዕራብ ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ ቤልጂየም፣ ኔዘርላንድና ሉክሰምበርግ ናቸው:: ሰኔ 1/1973 ዓ.ም. ሦስት አዳዲስ አባል ሀገራት /ታላቋ ብሪታኒያ፣ አየርላንድና ዴንማርክ/ ከቡድኑ ጋር በመቀላቀል የአባላቱን ቁጥር ወደ ዘጠኝ አሳደጉት:: በ1979 ዓ.ም. በሰነዱ ላይ ፊርማዋን ያኖረችው ግሪክ ደግሞ ጥር 1/1981 ዓ.ም. አባል ሆነች:: ግሪክ የጥንታዊው ሮም ግዛተ-አፄ አካል እንደ መሆኗ መጠን፣ የጋራ ገበያው አባል መሆኗ የሚጠበቅ ነው::

ኅብረቱ በሮም ስምምነት ላይ መገንባቱ የአጋጣሚ ጉዳይ ነው? ስምምነቱ የአውሮጳ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ መዲና በሆነችው ብራሰልስ ለምን አልተፈረመም? እርግጥ ነው፣ የመጀመሪያው ስብሰባ የተካሄደው በሮም ነው:: ስብሰባው በፓሪስ፣ ፍራንክፈርት ወይም ቦን ያልተካሄደው ለምንድን ነው? ምክንያቱም የዘመናችን ፌደሬሽን ከሮም መውጣት ስላለበት ነው፤ ስለዚህም፤ ለምሥረታው ሮም ተመርጣለች::

የጋራ ገበያው ራሱ ባወጣው የኅትመት ውጤት ላይ የአውሮጳ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብን ከመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢቶች በማያያዝ፣ «የአውሮጳ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የሮም ስምምነት ይህ የመጨረሻው ዘመን ግዛት አዲስ የሮም ግዛተ-አፄ እንደሆነ የሚነግሩንን የትንቢተ ሕዝቅኤልን፣ የትንቢተ ዳንኤልንና የዮሐንስ ራእይን መጻሕፍት ትርጉሞችን የሚደግፍ ነው» ብሏል::

የአውሮጳ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ያወጣው የኅትመት ውጤት በኅብረቱና በመጽሐፍ ቅዱስ በተተነበየለት የዘመን ፍጻሜው ዳግም ያንሰራራው የሮም ግዛተ-አፄ መካከል ያለውን ግንኙነት አምኖ መቀበሉ በእውነቱ የሚያስገርም ነው::

አውሮጳን የማዋሐዱ ሥራ ትልቅ ጥረትን የሚጠይቅ ቢሆንም፣ ኃይል 13 በዚህ ረገድ እገዛውን ለመስጠት ምንጊዜም ዝግጁ ነው::

Scanned with CamScanner

ዐሥሩ የአውሮጳ ሀገራት በታሪካቸው በተደጋጋሚ ተለያይተው የቆዩ ቢሆኑም፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ የፋይናንስ፣ ፖለቲካዊና ወታደራዊ አንድነት የመመሥረቱ ጥረት እየተጠናከረ ነው:: በ1979 ዓ.ም. የጋራ ገበያው ሀገራት ቀጥተኛ የፓርላማ ምርጫ ተካሂዶ የአውሮጳ ፓርላማ ተቋቁሟል::

እስፔይንና ፖርቱጋል በጥር 1986 ዓ.ም. የአውሮጳ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ አባል በመሆናቸው የጋራ ገበያው 12 ሀገራት ያቀፈ ኮፌዴሬሽን ሆኗል:: ምሥራቅ ጀርመን በ1990 ዓ.ም. ከምዕራብ ጀርመን ጋር ዳግም ስትቀላቀል የጋራ ገበያው ይበልጥ ተጠናክሯል:: ሌሎች ሀገረት ከጋራ ገበያው ጋር ሊቀለቀሉ ወይም ሊወጡ ቢችሉም፣ የዮሐንስ ራእይ 17:12-13 በስተመጨረሻ ላይ «አሥር ነገሥታት» ሉዓላዊነታቸውን ለ«አውሬው» አሳልፈው እንደሚሰጡ ይነግረናል:: እነኝህ 10 መንግሥታት የቀረውን የዓለም ክፍል ለአዲሱ የዓለም ሥርዓት እንዲንበረከኩ ለማስገደድ የኃይል 13 የሥልጣን መሠረት ሆነው ያገለግላሉ::

የ12ቱ ሀገራት አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት ከ35 ሚሊዮን በላይ ነው:: ከፌዴሬሽን ውጭ ለሚደረግ ጉዞ የሚውል የጋራ ገበያው ፓስፖርት ለአውሮጳ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ «ዜጎች» እየተሰጠ ነው::

ሌሎች ሀገራት የጋራ ገበያው ተባባሪ አባላት መሆን ይችላሉ:: የዚህ በኢኮኖሚ፣ ፖለቲካና ሃይማኖት የተሳሰረ ግዛት ንግድ ዓለም አቀፋዊ ገጽታ መላበስ እንዳለበትም የሚታወቅ ነው::

«አሕዛብ ሁሉ ከዝሙትዋ ቁጣ ወይን ጠጅ የተነሣ ወድቀዋልና፣ የምድርም ነገሥታት ከእርስዋ ጋር ሴሰኑ የምድርም ነጋዴዎች ከቅምጥልነትዋ ኃይል የተነሣ ባለ ጠጋዎች ሆኑ ብሎ ጮኸ::» (የዮሐንስ ራእይ 18:3)

በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 18 ግዛቱ ባቢሎን የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል:: «ባቢሎን» የሰይጣንና የጥፋት ልጁ ግዛት ተምሳሌታዊ መጠሪያ ስም እንደሆነ መዘንጋት የለብንም::

በለንደን ታትሞ የሚወጣው ዴይሊ ሚረር ጋዜጣ እንደሚለው፣ ከሁሉ የበለጠ ዲፕሎማሲያዊ ጥበብና ግርማ ሞገስ ያለው ሰው በጋራ ገበያው አባል ሀገራት ውስጥ በምሥጢር እየተፈለገ ነው:: ሀገራቱ

በግለሰቡ ማንነት ዙሪያ መስማማት ከቻሉ፣ የአውሮጳ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ኅብረ-ብሔራዊነትን የሚያንጸባርቅ ዋነኛው ተምሳሌት ይሆናል::

በአሁኑ ወቅት የአውሮጳ ማኅበረሰብ ፓርላማ የሚሰበሰበው በስትራስቡርግ ነው:: የጋራ ገበያው አስተዳደራዊ መዲና ግን ብራሰልስ ናት:: በስተመጨረሻ ላይ መዲናዋ ወደ ሮም እንደምትዛወር አጠራጣሪ አይደለም:: ከዚህ በተጨማሪም፣ ሮም «የመንበረ-ፓፓው»፣ ማለትም የሮም ካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን ርእሰ-ሊቃነ-ጳጳሳት፣ መቀመጫ እንደ መሆኗ መጠን፣ የጋራ ገበያው መዲና አድርገን ልንቆጥራት እንችላለን:: የሮም ካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን የጋራ ገበያው ሀገራት አብላጫው ሕዝብ የሚከተለው ሃይማኖት ነው:: የእንግሊዝ አንግሊካንና የጀርመን ሉተራን ቤተ-ክርስቲያን በአሁኑ ወቅት እያደገ የመጣውና ወደፊት ያለጥርጥር በፓፓው በሚመራው የአንድ ዓለም «ክርስቲያን» ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ እየታቀፉ ነው:: በጥር 1977 ዓ.ም. የአንግሊካን-ሮማ ካቶሊክ ዓለም አቀፍ ኮሚሽን ይፋ ባደረገው ሰነድ ፓፓው ወደፊት የሚቋቋም ማንኛውንም የአብያተ-ክርስቲያናት ኅብረትን ይመራሉ::

በአሁኑ ዘመን እየታየ ያለው ዓለም አቀፋዊ የክርስትና ንቅናቄ በአጋጣሚ የተፈጠረ አይደለም:: የዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 17 ትንቢት በክፋት ሃይማኖታዊ ሥርዓትና በክርስቶስ ተቃዋሚ የአውሬው ግዛት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያሳይ በመሆኑ ንቅናቄው የምሥጢረ 666 አካል ነው::

«በመንፈስም ወደ በረሃ ወሰደኝ፤ የስድብም ስሞች በሞሉበት፣ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ:: ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጐናጸፋ ነበር፣ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቆችም ተሸልማ ነበር፣ በእጅዋም የሚያስጸይፍ ነገር የዝሙትዋም ርኩሰት የሞላበትን የወርቅ ጽዋ ያዘች፤ በግንባርዋም ምሥጢር የሆነ ስም፦ ታላቂቱ ባቢሎን የጋለሞታዎችና የምድር ርኩሰት እናት ተብሎ ተጻፈ::» (የዮሐንስ ራእይ 17:3-5)



Scanned with CamScanner

በዚህ ምዕራፍ የተጠቀሰው «ቀይ አውሬ» በምዕራፍ 19 ካነበብነው ግዛት ጋር አንድ ነው:: ይኸው ግዛት ቀደም ሲል የነበሩት ሰይጣናዊ ግዛቶች በሙሉ ማከተሚያ የሆነው ባለ ዐሥር ቀንዱ ፌደሬሽን ነው:: «ታላቂቱ ባቢሎን» የሚል መጠሪያ የተሰጣት ሴት፣ የእነኝህን ሰይጣናዊ ግዛቶች ሃይማኖታዊ ገጽታን የምትወክል ናት:: በእኩይ ሰዎችና በሰይጣን ግዛቶች ያለውን የክፋት ሥርዓት የምትወክል ናት::

በትንቢቱ መሠረት፣ «የጋለሞታዎች እናት» በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተቀምጣለች:: በታላቁ የአውሬው ግዛት ላይ ግርማ ሞገስ ተላብሳ እየጋለበች ነው:: «ጋለሞታዋ» የምትወክለው በተለይ በክፋት የተሞላውንና ሃይማኖቱን የከዳውን የክርስትና እምነትን ነው:: የዓለም የአብያተ-ክርስቲያናት ምክር ቤት፣ ቫቲካንና የአዲስ ዘመን ንቅናቄ (ኒው ኤጅ ሙቭመንት) ለመመሥረት እየሞከሩ ያሉት የዓለም ሃይማኖቶች ኮፌዴሬሽንም የዚህ ሂደት የመጨረሻው ውጤት ነው:: (የምሥረታው ሂደት ተጠናክሮ እንደቀጠለ ነው::)

ለበርካታ ምዕተ-ዓመታት ከሮማ ካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን ተነጥሎ የቆየው የግሪክ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን በአሁኑ ወቅት የፓፓውን ሥልጣን ተቀብሏል:: ርእሰ-ሊቃነ-ጳጳሳት ፖል የቁስጥንጢንያ ሊቀ-ጳጳስ ላቀረቡት አስታራቂ መግለጫ በምላሹ በታኅሣሥ 1975 ዓ.ም. የግሪክ ቤተ-ክርስቲያን ተወካይን እግር ተንበርክከው ስመዋል::

ብዙ ሰዎች ፓፓው የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው ሲሉ አስበዋል፣ አስተምረዋልም:: ለዚህም አመለካከታቸው የሚያቀርቡት የመከራከሪያ ሐሳብ በፓፓው ዘውድ ላይ የተቀረጸውን ማዕረግ አኃዛዊ ዋጋን ነው:: «በፓፓው ዘውድ» ላይ የሰፈረው VICARIVS FILEII DEI የሚለው ሐረግ «የእግዚአብሔር ልጅ ምትክ» የሚል ትርጉም አለው::

በመሠረቱ፣ በአኃዝነት የሚያገለግሉ የሮማውያን ፊደላት ስድስት ብቻ ነበሩ:: እነኝህም I-1፣ V-5፣ X-10፣ L-50፣ C-100 እና D-500 ናቸው:: (የኋላ ኋላ 1000ን የሚወክለው M ተጨምሯል::) እነኝህ ስድስት ቁጥሮች ሲደመሩ የሚሰጡን ዋጋ 666 መሆኑ የአጋጣሚ ጉዳይ ይሆን? የአብላጫው የዓለማችን ክርስቲያን መሪ የሆኑትን ፓፓ ማዕረግ ስንመለከት ደግሞ በዘውዳቸው ላይ የሰፈረው ጽሑፍ በሮማውያን ፊደላት መሠረት ሲደመር 666 ይሰጠናል::



Scanned with CamScanner

| | | |
|---|---|---|
| V-5 | F-0 | Ḋ-500 |
| I-1 | I-1 | E-0 |
| C-100 | L-50 | <u>I-1</u> |
| A-0 | E-0 | 501 |
| R-0 | I-1 | 112 |
| I-1 | <u>I-1</u> | <u>53</u> |
| V-5 | **53** | **666** |
| <u>S-0</u> | | |
| 112 | | |

በእርግጥ፣ ይህ ስሌት ፓፓው የክርስቶስ ተቃዋሚ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አይደለም:: በዮሐንስ ራእይ 13:18 ላይ 666 የክርስቶስ ተቃዋሚ ስም አኃዝ እንደሆነ እንመለከታለን:: የክርስቶስ ተቃዋሚ እስካሁን ድረስ ያልተገለጠ የጥፋት ልጅ በመሆኑ ፓፓው የክርስቶስ ተቃዋሚ አይደሉም:: የሚገለጠውም መንፈስ ቅዱስ እውነተኛ አማኞችን ከዚህ ዓለም ነጥሎ ከወሰዳቸው በኋላ ነው:: ሆኖም፣ ፓፓው በአውሮጳ ኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ምሥረታ እንዳደረጉት ሁሉ በዓለም ቤተ-ክርስቲያን መሪነታቸው ለክርስቶስ ተቃዋሚ መነሣት ጉልህ ሚና መጫወታቸው አይቀርም::

ዙፋናቸውን ከጥንታዊው የሮም ግዛተ-አፄ ጋር የሚያስተሳስረው ሌላኛው የፓፓው PONTIFEX MAXIMUS ማዕረግ ነው:: ይህን ማዕረግ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመበት የባቢሎናውያን ኑፋቄ በሮም ተመሠረተ በኋላ የመጀመሪያው የሮም አረማዊ ሊቀ-ካህናት ነው:: ኋላ ኋላ ማዕረጉ ለጁሊየስ ቄሳር ሲሰጥ፣ በቀጣይነትም እስከ ታላቁ ቆስጠንጢኖስ ድረስ ያሉት የሮም ነገሥታት ተጠቅመውበታል:: ቆስጠንጢኖስ ክርስትናን እንደተቀበለ እምነቱን የግዛቱ ኦፊሴላዊ ሃይማኖት የሚያደርግ አዋጅ አውጥቷል:: ይህን ተከትሎ ክርስቲያኖች ላይ ይደርስ የነበረው ሥቃይና እንግልት ቢቆምም፣ ...ዋሚ የሮማውያን «ምሥጢራት» የቤተ-ክርስቲያኗ ትውፊት አካል ...ነዋል:: የኋላ ኋላ Pontifex Maximus የሚለው ማዕረግ «...ንጉሠ-ነገሥት»፣ ማለትም ፓፓው፣ ሊተላለፍ ...ተቀደሰችዋ ሮም ...

...ኋል::



Scanned with CamScanner

የባቢሎን ሃይማኖት፣ ማለትም የዓለም ቤተ-ክርስቲያን፣ ፍጹሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተተንብየዋል::

«ያየሃቸውም አሥር ቀንዶችና አውሬው ጋለሞታይቱን ይጣላሉ፤ ባዶዋንና ራቁትዋንም ያደርጓታል፣ ሥጋዋንም ይበላሉ፣ በእሳትም ያቃጥሉአታል::» (የዮሐንስ ራእይ 17:16)

ለበርካታ ዓመታት የሰይጣን መሣሪያ ሆኖ ያገለገለው የክፋት ሃይማኖት አምልኮተ-ሰይጣን በመላው ዓለም ዙሪያ ሲመሠረት ጊዜው ያልፍበታል:: እንደ ሌሎች የኃይል 13 መሣሪያዎች ሁሉ ጠቃሚነቱ ስለሚያበቃ ይወገዳል:: በእሳትም ይቃጠላል:: የኃጢአት ዋጋ ይኸው ነው:: ሰይጣን ማንኛችንንም ለዓላማው ማስፈጸሚያነት ከተጠቀመብን በኋላ ያጠፋናል:: ስለዚህም፣ በሰይጣን መዳፍ ሥር ላለመውደቅ ለራሳችን ቃል መግባት ይኖርብናል::



Scanned with CamScanner

# ምዕራፍ 15

# ዘመናዊነት

«በውስጥዋ ያሉ ነቢያት እንደሚጮኽና እንደሚናጠቅ አንበሳ አንድ ሆነው ተማማሉ፤ ነፍሶችን በልተዋል፤ ብልጥግናና ሀብትን ወስደዋል፤ በውስጥዋም መበለቶችን አብዝተዋል... ነቢያት በሐሰት ትንቢት ይናገራሉ፣ ካህናትም በእነዚህ እጅ ይገዛሉ፣ ሕዝቤም እንዲህ ያለውን ነገር ይወድዳሉ፤ በፍጻሜውስ ምን ታደርጋላችሁ::»
(ትንቢተ ሕዝቅኤል 22:15፤ ትንቢተ ኤርሚያስ 5:31)

የዘመናችን መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ክርስቲያኖች ከበርካታ ዘመናዊ «የክርስቲያን» ሃይማኖት ሊቃውንት አንደበት በሚወጣው ፍጹም የማይረባ ነገር በድንጋጤ ክው እንዳሉ ነው:: ተደናግጠው ሲያበቁም፣ «በግልጽ ከተቀመጠው የእግዚአብሔር ቃል በአሁኑ ዘመን ማፈንገጡ እየበዛ የመጣው ለምንድን ነው? በክርስትና ዓለም ውስጥ የሚገኙ የክርስቲያን መሪዎች በሚያስደነግጥ መልኩ ሃይማኖታቸውን እየካዱ ያሉት ለምንድን ነው?» ብለው እየጠየቁ ነው::

በእርግጥም ሁኔታው አስደንጋጭ ነው:: ለምሳሌ ያህል፣ የተከበሩ ቄስ ቤን ስሚል የተባሉ የተባበሩት ክርስቲያኖች ቤተ-ክርስቲያን አለቃ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ያነሡበትን አባባል እንመልከት:: ስሚል በክርስቲያኖች ላይ ሲያሾፉ፣ «ከጭቃ በተሠራ ሰው፣ ውኃ ላይ በተንሳፈፈ መካነ-አራዊት፣ ውኃ ላይ በተራመደው ኢየሱስ፣ ውኃን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ በቤት ውስጥ ጠመቃ መለኮታዊነትን ባሳየው የእግዚአብሔር ልጅ፣ እንዲሁም በኬፕ ኬኔዲ እንደሚነሡት ሮኬቶች ወደ ሰማይ ባረገው ኢየሱስ ማመናቸውን የሚቀጥሉ ናቸው» ብለዋል::

በርካታ የዘመናችን ሰባኪያን የዘመናዊነት፣ የሊበራሊዝም፣ የተሐድሶ ኦርቶዶክስና የኢ-አማኒነት ፍልስፍና አራማጆች ብቻ አይደሉም:: ብዙዎቹ ኢ-ግብረ-ገብነትን፣ ዝሙትንና ብልሹነትን፣ እንዲሁም ሥርዓት አልበኝነትንና አብዮትን በግልጽ የሚያበረታቱ ናቸው::



Scanned with CamScanner

መናፍቅነትና በእግዚአብሔር አለማመን በመሰበኪያ ተቀባይነት ሊያገኙና በቤተ-ክህነት ትምህርት ቤቶች እንደ ትምህርት ሊሰጡ የቻሉት እንዴት ነው? ክርስቲያናዊ ድርጅቶች በባሕር ማዶ የሚካሄዱ ሸምቅ ውጊያዎችን በገንዘብ የሚደግፉትና በሀገር ውስጥ ወሲባዊ ልክስክስነትን የሚያስራጩት ለምንድን ነው? ግብረ-ሰዶማውያን ቢጤዎቻቸውን ከኃጢአታቸው ለመዳን ሳይሆን ለአስከፊው ድርጊታቸው መልካም ስም ለማትረፍ በመላው ዓለም ዙሪያ የ«ግብረ-ሰዶማዊ» አብያተ-ክርስቲያናት መረብ የዘረጉት ለምን ይሆን?

በአብያተ-ክርስቲያናቱ የሚንጸባረቀውን ዘመናዊነት፣ ክህደተ-ሃይማኖትና ኢ-ግብረ-ገብነት «የዘመኑ መንፈስ» ብለን ልንፈርጀው እንችላለን:: ይሁንና፣ ሁኔታው እንዲሁ በአጋጣሚ የተፈጠረ አይደለም:: በሚገባ የታቀደ የ666 ሴራ አካል ነው:: እዚህ ላይ የኢሉሚናቲን ሁለት ዓላማዎች ማንሣቱ ተገቢ ይሆናል::

1. እግዚአብሔርን ከመንግሥተ-ሰማያት፣ የክርስትና ሃይማኖትን ከምድር ማስወገድ::
2. ወጣቱን ምግባረ-ብልሹ ማድረግና ሕይወቱ በወሲብ ዙሪያ እንዲያጠነጥን ማድረግ:: አስጸያፊና ነውረኛ ሥነ-ጽሑፍ ማሰራጨት:: ግብረ-ሰዶማዊነትንና ዝሙትን ማበረታታት::

ባለፉት ሁለት መቶ ዓመታት ኃይል 13 ከቀረው ምሥጢራዊ መርሐ-ግብሩ ጋር እነኝህን ሁለት ነጥቦች ሲያስፋፋ ቆይቷል:: በአሁኑ ዘመን በዙሪያችን የምንመለከተው ነገር ሁሉ የዚሁ የታቀደ ሴራ ውጤት ነው::

## የኢሉሚናቲ ትምህርተ-ሃይማኖት

አዳም ዌይስሆፕት ማኒኬይዝም የተሰኘው የግብፅ ስውር ጥበ… መቅሰሙን ቀደም ሲል አንብበናል:: ስለዚህም፣ ዌይስሆፕ… የአምልኮተ-ሰይጣን ተከታይ ነው:: ይሁንና፣ «ጥልቅ ዕውቀት ያለ… ሴረኛ» እንደ መሆኑ መጠን፣ ለመሠረተው ምሥጢራዊ ማኅበ… «ክርስቲያናዊ» ሽፋን በመስጠት የአውሮጳ ፍሪሜሶናችን እጁ ውስ… አስገብቷቸዋል::



Scanned with CamScanner

ኢሉሚናቲ የካህን ወይም የቀሲስ ደረጃ ያለው ሲሆን፣ ቄይስሆፕትም «ሜይሶኒክ ክርስትና» የሚል መጠሪያ የሰጠውን «ኖናውንና ሐዋሪያዊውን የክርስትና ሃይማኖት» እሰብካለሁ ባይ ነበር:: እንደ ቄይስሆፕት አባባል፣ ክርስትናን በሚመለከት አዲስ ግኝቶቹ ለበርካታ ምዕተ-ዓመታት በዘለቀው ተቋማዊ ሃይማኖት ተደብቀው ቆይተዋል::

የቄይስሆፕት ትምህርተ-ሃይማኖት በመሠረቱ «ሁልአምላክነት» ወይም «ተፈጥሮአዊነት» ነው፤ ይህም ሃይማኖታዊ እውነት በራእይ ሳይሆን ከተፈጥሮ የሚገኝ ነው የሚል ፅንሰ-ሐሳብን ያዘለ ነው:: «እግዚአብሔር» በሁሉም ነገር ውስጥ አለ፣ እንዲሁም ዩኒቨርስ «እግዚአብሔር» ነው የሚል አስተምህሮ ነው:: በመሠረቱ ሁልአምላክነት የመለኮታዊ ፍጡር መኖርን የሚክድ እንደ መሆኑ መጠን፣ ኢ-አማኒነት ነው:: ግላዊነት ብዙም ትኩረት የማያገኝበትና ሁሉም ሰው የዩኒቨርሱ አካል የሆነበት የጋርዮሽ ርዕዮተ-ዓለምን የሚያመላክት ነው:: በዚህ ፍልስፍና መሠረት የሰው ልጅ ከአፈር እንደ መጣ ሁሉ ወደ አፈር (ተፈጥሮ) ይመለሳል::

ቄይስሆፕት ይህን ፅንሰ-ሐሳብ ያምንበታል ማለት ባይቻልም፣ የሰው ልጅን ከክርስቶስ ለማራቅ ፍልስፍናውን ተጠቅሞበታል:: የዓለማችን ሕዝብ በሙሉ በአመንክንዮ «ዕውቀትን መቅሰም» እንዳለበትና በአንድ ቤተሰብ፣ በአንድ ሃይማኖትና በአንድ መንግሥት ሥር ባንድነት እንዲሰለፍ መስበኩን የሕይወቱ አንድ ዓላማ አድርጎት ነበር::

ከዚህ በተጨማሪም፣ ማንኛውም የሲቪል ነጻነት እኩል ነው የሚለውን ሥርዓት አልበኝነትን አስተምሯል:: የኢየሱስን ስም በመጥራት መጽሐፍ ቅዱስን አጣምሞ በማቅረብ ይህን ፅንሰ-ሐሳብ ተገቢ አድርጎ ለማቅረብ ሞክሯል:: (ክርስቶስ «አብዮተኛ» ወይም «የመጀመሪያው ኮሙኒስት» ነበር የሚሉት ወገኖችም ይህንኑ የቄይስሆፕትን አካሄድ ነው የተከተሉት:: በእውነቱ፣ ክርስቶስ አብዮተኛም ሆነ የመጀመሪያው ኮሙኒስት አልነበረም::)

Scanned with CamScanner

ዌይስሆፕት፣ «የማኅበራችን አውራ የሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው ዓለማችን ፍጹም ሥርዓት የለሽ በሆነችበት ወቅትና ለዘመናት በባርነት ቀንበር ይማቅቅ በነበረ ሕዝብ መኻል ነው። የአመክንዮን ትምህርት ለዚሁ ሕዝብ አስተምሯል። በዚህ ረገድ ይበልጥ ውጤታማ ለመሆን ሃይማኖትን፣ ማለትም በወቅቱ የነበሩ አመለካከቶችን፣ በመሣሪያነት ተጠቅሟል። ብልጠት በተሞላው መልኩም ምሥጢራዊ አስተምህሮዎቹን ከሕዝቡ ሃይማኖትና ልማድ ጋር አጣምሯቸዋል። ትምህርቱን ያስተማረው በዚህ ዘዴና ምሳሌዎችን በመጠቀም ነው… ነጻነትንና እኩልነትን የአስተምህሮዎቹ ትልቁ ዓላማ አድርገን ከወሰድናቸው… በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ ሊገባን ይችላል፤ ኢየሱስን እንደ የባሮች መድኃኒት ሆኖ ይታያል። የሰው ልጅ የንጹሕ ተፈጥሮ መገለጫ ከሆኑት ነጻነትና እኩልነት ተራርቋል። በራሱ መጥፎ ምግባር ሳቢያ በባርነት እየማቀቀ ነው። ይህም የኃጢአት ሁሉ የመጀመሪያው ነው። የጸጋ ግዛት ከአመክንዮ በሚገኝ ዕውቀት ሊገኝ የሚችል ተሐድሶ ነው… አዲሱ ትውልድም ይኸው ነው። የሰው ልጅ በመንግሥት ሥር ሲኖር ኃጢአቱ ይበዛል፣ ዋጋ ያጣል፣ እንዲሁም ተፈጥሮው ይጐድፋል» ሲል ጽፏል።

ይኸው የጥፋት ልጅ የማሳሳቻ ዘመቻውን ስሌት አስመልክቶ ለአንድ ውስጠ-ዐወቅ ሲጽፍለት፣ «የቀሲስ ደረጃዬ የፈጠረልኝን አክብሮትና ኩራት እንዲህ ነው ብዬ ልነግርህ አልችልም፤ ይህ ደግሞ በጣም አስደሳች ነው። በአሁኑ ወቅት በማኅበሩ ውስጥ የታቀፈ አንድ የፕሮቴስታንት ካህን በዙሪያው ያለው ሃይማኖት የክርስትና እውነተኛ ትርጉም መሆኑን አምኖ ተቀብሏል። የሰው ያለህ! የሰው ያለህ! አንተን ማሳመን የማይቻል ነገር አለ? የአዲስ ሃይማኖት መሥራች እሆናለሁ ብሎ አንድም ያሰበ ሰው የለም» ብሎታል።

የኢሉሚናቲ ማኅበርን ካጋለጡት ቀደምት ሥራዎች መካከል አንዱ በስኮትላንድ፣ ኤዲንበርግ ነዋሪ የነበረው ፕሮፌሰር ጆን ሮቢንሰን በ1798 ዓ.ም. የጻፈው ፕሩፍስ ኦቭ ኤ ኮንስፒረሲ መጽሐፍ ነው። ሮቢንሰን በዚህ መጽሐፉ ላይ፣ «ፍሪሜሶንሪና ክርስትና ከተቀየጡ በኋላ ክርስትና ለሌላ ዓላማ እንዲውል ብቻውን ተጣምሞ

ቀርቧል፡፡ ቄይስሆፕት በቀጣይነት ክርስትናን ሙሉ በሙሉ ማሽቀንጠር በተፈጥሯዊ ሃይማኖትና ኢ-አማኒነት ተክቶታል...» ሲል ጽፏል፡፡

ፕሮፌሰር ሮቢንሰን ይኸው የሁልአምላክነት አስተምህሮ ከቄይስሆፕት ኢሉሚናቲ ማኅበር ጋር የቅርብ ትስስር በነበረው ታዋቂው የሃይማኖት ዶክተር ካርል ፍሬድሪክ ባህርድት እንዴት እንደተሰራጨ በመጽሐፉ ውስጥ አስረድቷል፡፡ ከባህርድት ሥራዎች መካከል አንዱ የሆነው ቤተር ዛን ሆረስ «የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪካዊ ሰነድነት ወይም የፈጣሪን ሐሳብ ራእይነትና የሰው ልጅ የወደፊት ተስፋ ለማጥፋት ያለመ ነው፡፡» ይኸው «አዲስ» አስተምህሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ «በሁሉም የጀርመን ክፍሎች ተስፋፍቷል፡፡» ታዲያ፣ ጀርመን የዘመናዊነት ዋነኛው መቀመጫ መሆኗ ሊገርመን ይገባል?

ከዚህን ጊዜ ወዲህ የኢሉሚናቲ አስተምህሮዎች ፕሮቴስታንትንና ካቶሊክን ጨምሮ በበርካታ አብያተ-ክርስቲያናት ሰርጾ ገብቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ የዛሬ ዘመን ዘመናዊነት፣ ሊበራሊዝምና ህልውናነት ፍልስፍናዎች አካል ሆኗል፡፡ የዚህ እምነት የለሽነት ፍልስፍና ሌላኛው መገለጫ «እግዚአብሔር ሞቷል የሚለው ሥነ-መለኮት» ነው፡፡

«ከተሐድሶው ወዲህ የፕሮቴስንት ቤተ-ክርስቲያን ታላቁ የሃይማኖት ሊቅ» የሚል መጠሪያ የተሰጠው ጀርመናዊው ፍሬድሪክ ሽሌይርማርከር (1768-1834 ዓ.ም.) ለኢሉሚናቲ ማኅበር ሁልአምላክነት ፍልስፍና ምንጭ የሆነውን ፈላስፋ ቤኔዲክት ስፒኖዛ አሞግሶታል፡፡ በዚህም የራሱን ተፈጥሮአዊነት ፍልስፍናን ቀልጭ አድርጎ አስቀምጧል፡፡ ሽሌይርማርከር፣ «ተቀባይነት ያላገኘውን የተቀደሰውን ስፒኖዛ በክብር ልናስታውሰው ይገባል፡፡ ስፒኖዛ መንፈሳዊ ዓለምን በጠረኑ አውዶታል፤ ፈጣሪ የስፒኖዛ መጀመሪያና መጨረሻ ነው፤ ብቸኛውና ዘለዓለማዊ ፍቅሩ ከዩኒቨርስ ጋር ነበር፡፡ የዘለዓለማዊው ዓለም መስተዋት ውስጥ ራሱን ከመመልከቱም ሌላ፣ የዚሁ ዓለም መስተዋት እንደሆነ ተረድቶታል፡፡ ስፒኖዛ በሃይማኖትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ፍጡር ነው፡፡ በሕዝቡ መኻል ጐልቶና አቻ

የለሽ ሆኖ ይታያል። የጥበቡ ጌታ ቢሆንም፣ አንድም ደቀ-መዝሙር የለውም» ሲል አሞካሽቶታል።

ይህንኑ አስተምህሮ የተከተለ አንድ የካቶሊክ ሃይማኖት ሊቅ ፒየር ቴይልሃር ደ ሻርዳ ነው። ቴይልሃር «ሁልአምላካዊ ዝግመታዊ ለውጥ»ን የሚያንጸባርቅ «ሳይንሳዊ ክርስትና» አራማጅ ነበር። በዚሁ ዙሪያም፣ «ሳይንሳዊ ክርስትና ብዙ ነገር ነው፤ ሁሉም ንድፈ-ሐሳቦች፣ ሁሉም መላምቶችና ሁሉም ሥርዓቶች ሊንበረከኩለትና እውነት ሊሆኑ ከፈለጉ ሊረዱት የሚገባ አጠቃላይ ሁኔታ ነው። ዝግመታዊ ለውጥ እውነቷን በሙሉ ብሩህ የሚያደርግ ብርሃንና ሁሉም መሥመሮች ሊከተሉት የሚገባ እጥፋት ነው» ሲል ጽፏል።

የቴየልሃር ፈጣሪ «የክርስቲያን እግዚአብሔርና የማርክሲስት እግዚአብሔር» ድብልቅ ነው። የዘመናት የዓለም አብያተ-ክርስትናት ምክር ቤት «እግዚአብሔርም» ይህን የመሰለ ነው። በእርግጥ፣ ኃይል 13 እስከተመለከ ድረስ በማንኛውም ስም ቢጠራ ግድ የለውም።

## ዘመናዊ ክህደተ-ሃይማኖት

የኢሉሚናቲ/ኮሙኒስት «ሥነ-መለኮት» በፕሮቴስታንትና ካቶሊክ ተቋማት በጥልቀት ሰርጾ ከመግባቱ የተነሣ በመላው ዓለም ዙሪያ በሚገኙ የመስበኪያ ሰገነቶችና «ክርስቲያን» አካላት መጠነ-ሰፊ ክህደተ-ሃይማኖት እንዳለ ብናነብ ልንገረም አይገባም። ይህ ሁሉ የሆነው በአጋጣሚ አይደለምና።

በ19ኛው ክፍለ-ዘመን ማብቂያና በ20ኛው ክፍለ-ዘመን መግቢያ ለኢሉሚናቲ አስተምህሮ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረጉት ሁለት የሃይማኖት ሊቃውንት ዶክተር ዎልተር ሮውሸንቡሽና ዶክተር ሃሪ ኤፍ. ዋርድ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት በመተንተን እነኝህ ሁለት ምሁራን የ20ኛው ምዕተ-ዓመት «የሃይማኖት አብዮት» ዋነኞቹ አቀንቃኞች ሳይሆኑ አይቀሩም። የግል ድኅነት አስፈላጊነትን «በማኅበራዊ ወንጌል» ተክተውታል። የዓለም አብያተ-ክርስቲያናት ምክር ቤት በአሁኑ ዘመን እየሰበከ ያለው ይኸው «ወንጌል» ከዌይስሆት «ሰብአዊነት» የተለየ አይደለም። «ወንጌል» ለሰው ልጅ ማኅበራዊ ንቃትን ሰጪ መሣሪያ ነው።



Scanned with CamScanner

እኩይ ምግባሩን ያላቋረጠው ኃይል 13 በሮውሸንቡሽ ሥነ-መለኮት አማካኝነት «አዲስ ውል» አቅርቧል። በዚህ ውል መሠረት «ምድር ላይ የሚሰፍነው የእግዚአብሔር ግዛት» እግዚአብሔርንና መርሖዎቹን ወደ ጎን በመግፋት የሚመሠረት ይሆናል።

የሮቸስተር ሥነ-መለኮት ትምህርት ምሩቅ የሆነው ሮውሸንቡሽ፣ በዚሁ ተቋም በፕሮፌሰርነት አገልግሏል። አንድ የአብያተ-ክርስቲያናት ፌደራል ምክር ቤት የቀድሞ ፕሬዚዳንት፣ «ባለፉት 50 ዓመታት በአሜሪካ ቤተ-ክርስቲያን ሕይወትና አስተሳሰብ ዙሪያ ትልቁን ብቸኛ ተጽዕኖ ያሳደረው ዎልተር ሮውሸንቡሽ እንደሆነ ለእኔ ግልጽ ነው» ሲል በ1937 ዓ.ም. ስለ ሮውሸንቡሽ ምስክርነቱን ሰጥቷል።

ለዚህ «አዲስ ወንጌል» ዐቅምና ኃይል የሰጠው ዶክተር ሃሪ ኤፍ. ዋርድ ነው። የለየለት ኮሙኒስት እንደሆነ የሚታወቀው ዋርድ፣ ለ25 ዓመታት ከፍተኛ ተሰሚነት ባለው የኒው ዮርክ ዩኒየን ሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት የክርስቲያን ሥነ-ምግባር ፕሮፌሰር ሆኖ አገልግሏል። ይህን ትምህርት ቤት በገንዘብ የሚረዱትም ሮክፌለሮች ናቸው። ትምህርት ቤቱ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸውን ሰባኪዎችና የሃይማኖት ሊቃውንት ሳይሆን «ክርስቲያን ኮሙኒስቶችን» በማፍራት የታወቀ ነው።

ዶክተር ዋርድ ለዓለም አብያተ-ክርስቲያናት ምክር ቤት ምሥረታ ትልቅ ሚና የተጫወተው የአሁኑ ብሔራዊ የአብያተ-ክርስቲያናት ምክር ቤት ቀዳሚው የሆነውን የአብያተ- ክርስቲያት ፌደራል ምክር ቤት በማቋቋሙ ሂደት ትልቅ ሚና ተጫውቷል። ዋርድ ዴሞክራሲ ኤንድ ሶሻል ቼንጅ (1940 ዓ.ም.) በተሰኘው መጽሐፉ፣ «ሃይማኖት የሰው ልጅ ማኅበረሰብ ቀጣዩን እርንከን በሚያመጣው ትግል ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ግልጽ ነው» የሚል ትንቢት አዘል ጽሑፍ አስፍሯል። ዋርድ በዮሐንስ ራእይ 20፡1-5 የተቀመጠው ለ1000 ዓመታት የሚዘልቀው የክርስቶስ አገዛዝ ሳይሆን የክርስቲያን አንድነት ሚና ይጫወታል ብሎ እንደሚጠብቅ ጽፏል።
ንቅናቄ አዲስ ዓለም አቀፋዊ ሥርዓት በመመሥረቱ ረገድ ቁልፍ

ኸርበርት ኤ. ፊልብሪክ የተባለ አንድ የኤፍ.ቢ.አይ. ነጭ ሰባኽ በ1953 ዓ.ም. ከዩ.ኤስ. አሜሪካ ኮንግሬስ ፊት ቀርቦ በሰጠው የምስክርነት ቃል፣ «እዚህ ሀገር ያለውን ኮሙኒስት ፓርቲ እስትራቴጂና ታክቲክ በሚመለከት ፓርቲው በአሁኑ ወቅት በዩ.ኤስ. አሜሪካ ውስጥ ሃይማኖትን የመጠቀም እንጂ የማጥፋት እቅድ እንደሌለው ዐውቀናል» ሲል ተናግሯል።

የሁሉም ማለት ይቻላል ዘርአ-ክህነት ትምህርት ቤቶች የመስበኪያ ስገነቶች በወጣት ሰባኪያን የተሞሉ እንደ መሆናቸው መጠን፣ የሥነ-መለኮት ትምህርት ቤቶች ሃይማኖትን በመሣሪያነት ለመጠቀም በተነደፈው እቅድ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል። ዌይስሆፕት ፍሪሜሰኖችን መዳፉ ውስጥ እንዳስገባ ሁሉ፣ የዛሬ ዘመን ኢሉሚናቲዎችም የቤተ-ክህነት ትምህርት ቤቶችን እየተቆጣጠሩ ነው።

በእርግጥ፣ አሁንም ቢሆን ጽንፈኛ አቋም የሚያራምዱ አንዳንድ የቤተ-ክህነት ትምህርት ቤቶች አሉ። ይሁንና፣ «ከክርስቲያን የትምህርት ወምበር» የሚመነጨው ክህደተ-ሃይማኖት በአጠቃላይ በክርስትና ላይ ትልቅ ተጽዕኖ እያሳደረ ነው።

በክርስቶስ አምላክነትና በእግዚአብሔር ህልውና ላይ በተንኰል የተሞላ ጥቃት ከሰነዘሩት መካከል አንዱ ኤ.ጄ. አንገርስማ ነው። አንገርስማ የፕሬስቢቴሪያን ቤተ-ክርስቲያን በሚጠቀምበት ሃንድቡክ ፎር ክሪስቲያን ቢሊቨርስ መጽሐፉ ላይ፣ «ተከታዮቹ ኢየሱስን ለማወደስ በሚያደርጉት እውነተኛ ጥረት አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ነው ብለው ድርቅ ይላሉ። ይሁና፣ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ አንድም ጊዜ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አያውቅም» ሲል ጽፏል።

የክርስቶስ ደቀ-መዛሙርት ቤተ-ክርስቲያን ልሳን፣ «ደቀ-መዛሙርት በአጠቃላይ ኢየሱስ እግዚአብሔር የመሆኑን ሐሳብ በጭራሽ ሊቀበሉት አልቻሉም» ይላል። በሌላ በኩል፣ የሜቶዲስት ቤተ-ክርስቲያን ጳጳስ ጌራልድ ኬኔዲ፣ «የአዲስ ኪዳን ቃል በአጠቃላይ ሲወሰድ ስለ ክርስቶስ አምላክነት በጣም ብዙ ምስክሮችን

የያዘ ቢሆንም፣ የክርስቶስ አምላክነትን የሚከላከል ነው» ሲል ተናግሯል::

የዘመናችንን የሃይማኖት ሊቃውንት በሚመለከት ይህ ይበቃናል:: እነዚህ ሊቃውንት ከእግዚአብሔር ቃል ፊት ሲቆሙ ውሸታሞች መሆናቸው ይረጋገጣል፣ አሲያም በእንቶ ፈንቶ ነገር ግራ የተጋቡ ናቸው::

የእግዚአብሔር ቃል የማይነቀነቅ አለት ነው:: ከዚህ በተጨማሪም፣ እምነት ማጣትን እንደ የደነበረ በረሮ በጭለማው መኻል በሚገኙ መሸሸጊያ ስፍራዎች እንዲገባ የሚያደርገው ብርሃን ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስን አምላክነት በሚመለከት እንዲህ ብሏል::

«በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ:: ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር:: ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም::» (የዮሐንስ ወንጌል 1:1-3)

«ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ በእኛ አደረ፣ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው ክብር የሆነውን ክብሩን አየ::» (የዮሐንስ ወንጌል 1:14)

«ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፣ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው::» (የዮሐንስ ወንጌል 3:13)

«ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን ነው? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው:: ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም፤ በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው::» (የዮሐንስ መልእክት 1:: 2:22-23)

ለኃጢአታችን ሲል ደሙን በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ክርስቶስ እምነት መዳን በዘመነኞቹ ዘንድ በንቀት ዓይን እየታየ ነው:: ከሪቫይዝድ ስታንዳርድ ቨርሽን መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች መካከል አንዱ የሆነው ፍሬደሪክ ኤስ. ግራንድ ቤሲክ ክሪስቲያን ቢሊፍስ በተሰኘው መጽሐፉ፣ «የክርስቶስን ሞት እንደ 'ተማጽኖ' መግለጽ

በኃጢአት የለሽ ሰው ሞት ማባበል የሚቻል ቁጡ እግዚአብሔርን በግልጽ የሚጠቁም ነው:: የአዲስ ኪዳን ትርጉም ግን ይህ አይደለም... ኢየሱስ የእግዚአብሔር ይቅር ባይነት በራሱ ሞት ላይ የተመሠረተ እንደሆነ አንድም ጊዜ በተዘዋዋሪም ሆነ በግልጽ አልነገረንም» ሲል ጽፏል:: ግራንት ሃይማኖቱን የካደ ሰው ነው:: መጽሐፍ ቅዱስን በመተርጐሙ ሂደት እገዛ ቢያደርግም፣ በቀላል ቋንቋ የተጻፈውን ጽሑፍ መረዳት እንኳን አልቻለም::

«... በደም ይነጻል፤ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም::... ክርስቶስ በእጅ ወደተሠራች የእውነተኛይቱ ምሳሌ ወደምትሆን ቅድስት አልገባምና፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርስዋ ወደ ሰማይ ገባ:: እንዲህ ቢሆንም፣ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፤ አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአት ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል::... እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ፣ የብዙዎችን ኃጢአት ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሠዋ በኋላ፣ ያድናቸው ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት ይታይላቸዋል::» (ወደ ዕብራውያን 9:22፣24፣26፣28)

«ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፣ የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻል::» (የዮሐንስ መልእክት 1:: 1:7)

«በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፣ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና:: ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም::» (የዮሐንስ መልእክት 1:: 4:9-10)

«ለኃጢያት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፣ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢያታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ::» (የጴጥሮስ መልእክት 1:: 2:24)

ግራንት፣ ጴጥሮስና ዮሐንስ የኢየሱስን ትምህርትና ሥራ በደንብ አልተረዱም ብለን እንድናምን የሚፈልግ ይመስላል:: ምንም እንኳን



Scanned with CamScanner